ግዮን

ቅጽ ፭ ቁጥር ፬

ቪዥታፊ መጭሔት



ነፃ ፈቃድ (Free Will) vs ተወሳኝነት (Determinism)

የእኩልነት ቅዠት
ዮዲት አማኑኤል

ሶስተኛው አወዳደቅ
ሞሲሳ ደምሴ (ዶ/ር)

ተማ'ሎተ ሁለንተና
ደብተራው

አስመለጠኝ!
ሳምራዊት ንጉሤ

ሚያዝያ 2018

ግሼ

ባዕሊ ዪቪተ ፀፀፎሐተ

የዝግጅት ክፍል



ማውጫ

1 37

11 49

32

8 46

21

35

ነፃ ፈቃድ (Free Will) vs
ተወሳኝነት (Determinism)

ዘፈሐቆ እልፊት ወዘበት እልፊቱ

የእኩልነት ቅዠት
(ግለሰባዊነት፣ ካፒታሊዝም እና የዘመናዊ ዲሞክራሲ ቅራኔዎች)

ያላባቸው እጆች...

ቂም አናወርስም

(መወድስ)
ለአፈር ጌጡ ንጉስ

አስመለጠኝ!

ሶስተኛው አወዳደቅ

ተማ’ሎተ ሁለንተና

ዮናስ ታደሰ ዓለማየሁ ታዬ

ዮዲት አማኑኤል

ቴዎድሮስ የማነብርሃን

ነቢል አዱኛ

ሲልአምላክ አሰፋ

ሳምራዊት ንጉሤ

ሞሲሳ ደምሴ (ዶ/ር)

ደብተራው

ነፃ ፈቃድ (Free Will) vs ተወሰኝነት (Determinism)

በክፍል አንድ ላይ የነፃ ፈቃድ አቀንቃኞች “የፈቃድ ነፃነታችን መገኛ ቦታው የት ነው?” ለሚል ጥያቄ፤ ከፊሎቹ “ድርጊቶቻችን ላይ”፣ ከፊሎቹ “ፍላጎቶቻችን ላይ”፣ ሌሎቹ ደግሞ “ሐሳቦቻችን ላይ” እያሉ የሚሰጡት መልስ ከመልሶቻቸው መለያየት የተነሳ እርስ በራሳቸውም ቢሆን በትችት የሚነታረኩበትን ጉዳይ፥ እንደዚሁም ከተቀናቃኞቻቸው፥ተወስኖታውያን/ተወሳኝነታውያን (Determin-ists) የሚሰነዘርባቸው የሰላ ትችት እንዴት “የነፃ ፈቃድ መገኛ ቦታ—locus of free will” እሳቤአቸውን ክፉኛ ቅርቃር ውስጥ የሚያስገባባቸው እንደሆነ ተመልክተናል።

አሁን በዚህ ክፍል በ የተወሳኝነት መከራከሪያዎች ላይ የሚሰነዘሩትን ትችቶች እንመለከታለን።

Free Will Determinism

ነፃ ፈቃድ (Free Will) vs ተወሳኝነት (Determinism)

(ክፍል ሁለት)

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 1

2. በየተወሳኝነት መከራከሪያዎች ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶች (The Case Against Determinism)

2.1 አመክንዮአዊ ተቃርኖ እና/ ወይም ህፀፅ (Logical Contradiction and/or Fallacy)

በቅድሚያ የምንመለከተው “ነፃ ፈቃድ የሚባል ነገር ፈፅሞ የለም” የሚለው የተወሳኝነት ነጠላ-ሐሳብ (proposition) በራሱ በውስጡ የቋጠረውን አመክንዮአዊ ተቃርኖን ነው። ይኼውም በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ሰው “ነፃ ፈቃድ የሚባል ነገር ፈፅሞ የለም” ሲል ሊያውቀው የሚገባው ነገር ቢኖር፥ ይሄን ሐሳቡን ጨምሮ ሌላም ማንኛውም ዓይነት ሐሳብ ለሌላ ሰው በማስረዳት ማሳመን እንደማይቻለው ነው። ምክንያቱም የተወሳኝነት አቀንቃኞች እንደሚሉን፣ ሁሉም ነገር (ሐሳቦቻችን፣ ፍላጎቶቻችን እና ድርጊቶቻችን) ከእኛ ምርጫ እና ቁጥጥር ውጪ በሆኑ የመንስኤ እና ውጤት ሰንሰለቶች አማካኝነት አስቀድሞ የሚወሰን ከሆነ፥ ይዛችሁት የነበረው ሐሳብ ስህተት ስለሆነ (ለምሳሌ ስለ ነፃ ፈቃድ) እሱን ትታችሁ ሌላ (ለምሳሌ ተወሳኝነትን) ተቀበሉ ማለት አይቻልም። አሁንም ምክንያቱ እያንዳንዱ ሰው በአእምሮው ውስጥ የሚይዘው ሐሳብ (“ነፃ ፈቃድ የሚባል ነገር የለም” የሚል ሐሳብን ጨምሮ) ሊይዝ የሚችለው፣ በራሱ ነፃ ውሳኔ ሳይሆን፤ ከራሱ የአካባቢ እና አካላዊ የተፈጥሮ ሁኔታ አንፃር ከቁጥጥሩ እና ከምርጫው ውጪ በሆነ ሁናቴ አስቀድሞ በሚወሰን የመንስኤ እና ውጤት ሰንሰለት አማካኝነት የሚፈጠር ሐሳብ ነውና የሚሆነው። ማለትም አንድ ሰው፣ “ነፃ ፈቃድ አለ” ወይም ደግሞ፣ “ነፃ ፈቃድ የለም” ብሎ የሚቀበለው፥ ሐሳቦቹን በገዛ ፈቃዱ አውጥቶና አውርዶ መርጦና ወስኖ ሳይሆን፥ እንዲሁ እንደዚያ አይነት ሐሳብ እንዲቀበል ከእርሱ ቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁናቴ አስቅደሞ ስለተወሰነለት ነውና። በአጭሩ ለማስቀመጥ አንድ ሰው “ተወሳኝነት”ን እንዲቀበል ሲወሰንለት፥ ሌላው ሰው ደግሞ “ነፃ ፈቃድን” እንዲቀበል የማይወሰንለት ምክንያት አይኖርም።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ነፃ-ፈቃድ የሚባል ነገር ከሌለ “ትክክል” ወይም “ስህተት” የሚባሉ ፅንሰ-ሐሳቦች ራሱ ሊኖሩ አይችሉም። ነፃ ፈቃድ በሌለበት “ትክክል” ወይም “ስህተት” የምንለው ሐሳብ መናገር ከሞከርን አመክንዮአዊ ተቃርኖ ውስጥ እንገባለን። ለምሳሌ፣ አንድ ተወስኖታዊ ሰው (determinist)፣ “ነፃ ፈቃድ የለም” የሚል ሐሳብ ሲያቀርብ፣ በአንድ በኩል ይሄን አቋሙን እውነት እንደሆነ እንደሚያውቅ አድርጎ ነው የሚያቀርበው። በሌላ በኩል ደግሞ (ማለትም የራሱ የተወሳኝነት ሀልዮት እሳቤው የሚነግረን ደግሞ) ሐሳቦች
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 2

አእምሮው ላይ የሚፈጠሩት ከራሱ ፈቃድ እና ቁጥጥር በመነጨ አስቦና አሰላስሎ አመንጭቶአቸው ሳይሆን፣ ከቁጥጥሩ ውጪ በሆነ ሁኔታ አእምሮው ውስጥ አስቀድመው በተከናወኑ ሂደቶች አማካኝነት “ነፃ ፈቃድ የለም” የሚል የተወሳኝነት ሐሳብ ሊቀበል እንደቻለ ነው። እዚህ ጋር ነው እንግዲህ ተቃርኖው ያለው።

በአንድ በኩል የተወሳኝነት አቀንቃኙ፣ “ተወሳኝነት እውነት እንደሆነ አውቃለሁ” ሊለን ከሆነ፣ እዚህ እውነት ላይ ሊደርስ የቻለው ለተግባራቱ ሁሉ ኃላፊነት ከመውሰድ ለመሸሽ ሲባል ከኢ-ምክኑያዊ መግፍኤ ምክንያት (irrational mo-tive) በመነጨ የደረሰበት መደምደሚያ ሳይሆን፣ እውነትነቱ ላይ በማስረጃ (ev-idence) እና በማረጋገጫ (proof) ላይ ተመስርቶ የደረሰበት ነገር መሆኑን መቀበል ይኖርበታል። ይሄን ከተቀበለ ደግሞ ይህ ተወስኖታዊ ሰው የሆነ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ሲሞክር፣ ኢምክኑያዊ እና ምክኑያዊ አማራጭ መንገዶች ከፊቱ እንደሚደቀኑ ሆኖም ግን ምክኑያዊ መንገዱን መርጦ መደምደሚያው ላይ መድረስ የሚቻለው መሆኑን እንደሚቀበል ያሳያል። እንዲሁም ደግሞ ምክኑያዊዉን መንገድ ትቶ ኢ-ምክኑያዊውን መንገድ ሊመርጥ ይችል እንደ ነበር እና ይሄን ምርጫውንም በማይሳሳት መንገድ (infallibly) የሚከተለው ሂደት እንዳልሆነም ያሳያል።

በሌላ በኩል ግን የራሱ የተወሳኝነት ሀልዮቱ አንድ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ “ምክኑያዊ መንገድ ወይስ ኢ-ምክኑያዊ መንገድ” ብሎ ለመምረጥ የሚያስችል ነፃ የሆነ ምርጫ እንደሌለው ነው የሚናገረው። ይሄም ማለት ትክክል ወይም ስህተት የሚባል አማራጭ የለምና፣አእምሮአችን ውስጥ ከቁጥጥራችን ውጪ አስቀድመው (በመንስኤ እና ውጤት ሰንሰለት) በተከናወኑ ነገሮች የሚወሰን የተፈጥሮአዊ ሂደት ክንዋኔ ነውና ያለው፣”ምክኑይ” ወይም “ኢ-ምክኑይ” ተብሎ ሊፈረጅ የሚችል ሂደት አይሆንም ማለት ነው።

ብዙውን ጊዜ፣ “ነፃ ፈቃድ ከሌለ ሞራሊቲ የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም” የሚለው አባባል ምንጩም እዚህ ላይ ነው ያለው። ከላይ እንደተመለከትነው ነፃ ፈቃድ በሌለበት “ትክክል” ወይም “ስህተት” የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም። “ትክክል” ወይም “ስህተት” የሚባል ነገር ከሌለ ደግሞ “በጎ” ወይም “መጥፎ” የሚባል ነገር አይኖርም። “በጎ” ወይም “መጥፎ” የሚባል ነገር በሌለበት ደግሞ “ሞራላዊ” ወይም “ኢሞራላዊ” የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም።

በነገራችን ላይ ከላይ የተገለፀው ተወስኖታውያን የሚገጥማቸው አመክንዮአዊ ተቃርኖ በሎጂክ የህፀፅ ትምህርት ውስጥ የራስ-ነጠል ህፀፅ (fallacy of self-ex-clusion) በመባል ይታወቃል። ምናልባት ከላይ የተሰጠው ማብራሪያ ለመረዳት
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 3

አስቸጋሪ ሆኖ ቢገኝ በሚል (ምናልባት የእኔም የመግለፅ አቅም ማነስ ተጨምሮ፤ ኢፕስተሞሎጂያዊ የሆኑ ሐሳቦችን አውዱን በጠበቀ መልኩ በአማርኛ ቃላት መግለፅ ያን ያህል ቀላል ስላልሆነ) በአማራጭነት የተወስኖታውያኑ መክራከሪያ አመክንዮአዊ ችግርን በዚሁ በራስ-ነጠል ህፀፅ መነፅርም እንመልከተው እስቲ።

የራስ-ነጠል ህፀፅ (the fallacy of self-exclusion) የሚፈፀመው አንድ ሰው እየተናገረበት ስላለው ነገር ወይም ጉዳይ በዚያው ንግግሩ ሲቃረነው ነው። ወይም ደግሞ አቋሙን እየገለፀበት ያለው አረፍተ-ነገር አቋሙን ራሱን የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ የሚከሰት ህፀፅ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው፣ “እውነት የሚባል ነገር የለም” ብሎ ቢናገር፤ በውስጠ ታዋቂነት “እውነት የሚባል ነገር የለም” ብዬ ከተናገርኩት “እውነት” ውጪ ሌላ እውነት የለም ሊለን እየሞከረ ነው። ይሄም ማለት፣ “እውነት የሚባል ነገር የለም” የሚለው አባባል፣ የተናጋሪውን አረፍተ-ነገር ጨምሮ ለሁሉም አረፍተ ነገሮች የሚሰራ ወይም መስራት የነበረበት ቢሆንም ቅሉ፤ “እውነት የሚባል ነገር የለም” የሚለውን አባባሉን ግን ነጥላችሁ እንደ እውነት ተቀበሉልኝ የሚል ሐሳብ ነው። ሎጂኩን ከተከተልን ግን፣ እውነት የሚባል ነገር ከሌለ፣ “እውነት የሚባል ነገር የለም” የሚለውንም ንግግር እንደ እውነት ልንቀበለው አይገባም ማለት ነው። ይሄን የሎጂክ ተቃርኖ ለማለፍ በሚመስል መልኩ ነው እንግዲህ ብዙ ሰዎች “ከዚህ እኔ ከምናገረው እውነት ውጪ ሌላ እውነት የሚባል ነገር የለም” ሲሉ፣ “እውነት የሚባል ነገር የለም”፤ “ከዚህ እኔ ከምናገረው እርግጠኛነት ውጪ ሌላ እርግጠኛ የሚባል ነገር የለም” ሲሉ፣ “ማንም ስለ ማንኛውም ነገር እርግጠኛ ሊሆን አይችልም”፤ “ከዚህ እኔ ማወቅ ከቻልኩት እውቀት ውጪ ማወቅ አይቻልም” ሲሉ፣ “ትክክለኛ እውቀት ማግኘት የማይቻል ነገር ነው”... ወዘተ እያሉ ሎጂካል ነገር እንደተናገሩ ሁሉ ደረታቸውን ነፍተው ህፀፅ የተሞላ ንግግር የሚደሰኩሩት።

እናም እንደ ሳም ሐሪስ ያሉ ተውስኖታውያንም፣
“ሰዎች ባዮኬሚካላዊ የሁለንታ (universe)
መጫወቻ አሻንጉሊቶች ናቸው፤ ማንም ቢሆን
የሚያስበው ወይም የሚያደርገው ነገር መሆን
ከነበረበት ውጪ መሆን ይችል የነበረ ነገርን
አይደለም።ከቁጥጥሩ ውጪ አስቀድሞ የተወሰነለት
ነገር ነው።” ሲሉን፣ ለመሆኑ እራሳቸውን
እዚህ መከራከሪያ ውስጥ አካትተው ነው እንዲህ
የሚያወሩት? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። እነሱ
ራሳቸው (ተወስኖታውያኑ) ማንኛውም የሚያስቡት፣
የሚናገሩት ወይም የሚያደርጉት ነገር መሆን ከነበረበት ውጪ መሆን የማይችል
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 4

ክሆነ በሁለንታው ውስጥ ባሉ ባዮኬሚካላዊ መስተጋብሮች የሚዝዘወሩ የሁለንታው አሻንጉሊቶች ናቸው ማለት ነው? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። በዚህም እነሱ ራሳቸው የሁለንታው መጫወቻ አሻንጉሊቶች ከሆኑ፣ ንግግራቸው ሁሉ ከአለት ጋር እየተላተመ እንዳለ የወንዝ ፏፏቴ ድምፅ ከቁጥጥራቸው ውጪ በሆነ መስተጋብር አስቀድሞ የተወሰነ ተራ ጩኸት ወይም ትፋት ነው የሚሆነው። እነሱ ተነጥለው የሁለንታው አሻንጉሊቶች ካልሆኑ ደግሞ አሁንም ንግግራቸው እርባናቢስ ነው የሚሆነው። ምክንያቱም ከላይ በተመለከትነው የራስ-ነጠል ህፀፅ መንገድ፣ “እኔ የሁለንታው አሻንጉሊት ሆኜ ሳለሁ እውነትን መናገር እችላለሁ ሌሎቻችሁ ግን አስቀድሞ የተወሰነላችሁን ውሸት ነው የምታወሩት” የሚል የአመክንዮአዊ ተቃርኖ ልየታ መሀይምነት የተጠናወተው ቧልት ነው የሚናገሩት።

በተወስኖታውያን መከራከሪያዎች ላይ ብዙ አይነት አመክንዮአዊ ህፀፆችን ማንሳት ቢቻልም መሰረታዊው ህፀፅ ይኼው የራስ-ነጠልነት ህፀፅ ነውና በዚሁ ይብቃን። ተጨማሪ አመክንዮአዊ ህፀፆችን ለማወቅ ከስር በማስቀምጣቸው ማጣቀሻዎች ላይ ማየት ይቻላል።

በመቀጠል በክፍል አንድ ካየናቸው ሦስት የተወሳኝነት መከራከሪያዎች ውስጥ “መንስኤነትን (causality)” በሚመለከት የሚሰነዘርን ትችት እንመለከታለን። የተቀሩት ሁለቱን፣ “የነፃ ፈቃድ መገኛ ቦታ”ን በትክክል ለይቶ ያስቀምጣል የምለውን የአይን ራንድን እይታ በምዳስስበት የመጨረሻው ክፍል-ክፍል ሦስት ውስጥ እንዳስሳቸዋለን።

2.2 ስሁት የመንስኤነት (causality) አረዳድ
በክፍል አንድ እንደተመለከትነው፤ የተወሳኝነት አቀንቃኞች ነፃ ፈቃድን ከማይቀበሉባቸው ምክንያቶች አንዱ እና ዋናው፣ “ነፃ ፈቃድ የመንስኤነት ህግን የሚቃረን ወይም የሚጥስ ነው” የሚል መከራከሪያ በማቅረብ ነው። የመከራከሪያው ፍሬ ሐሳቡን በአጭሩ ለማስታወስ ያክል :-

“ሁሉም ኩነቶች አስቀድመው ከነበሩ ኩነቶች መንስኤነት፣ ሁሉም ድርጊቶች ደግሞ ከዚያ በፊት ለነበሩ ድርጊቶች ግብረ-መልሶች በመሆናቸው፣ አስቀድሞ የነበረ ኩነት መግፍኤ ያልሆነው “ነፃ” የሚባል ፈቃድ ሊኖር አይችልም። አስቀድመው በነበሩ ኩነቶች አስገዳጅ መግፍኤነት የማይከሰት ኩነትን ከሆነ “ነፃ ፈቃድ” የምንለው ደግሞ ነፃ ፈቃድ ሳይሆን መንስኤ አልባ፣ የዘፈቀደ ኩነት ነው የሚሆነው። የዘፈቀደ ኩነት ደግሞ በእኛ ፈቃድ የተደረገ ሳይሆን በአጋጣሚ ወይም ደግሞ በእድል የሚከሰት ነገር ነው የሚሆነው” የሚል ነው።
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 5

ተወስኖታውያን በዚህ መንገድ ሊከራከሩ የቻሉት በመንስኤነት ፅንሰሐሳብ ላይ ካላቸው ስሁት አረዳድ የተነሳ ነው። ያ ስሁት ግንዛቤአቸው ደግሞ፣ “ሁሉም ኩነቶች አስቀድመው በነበሩ ኩነቶች ግፊት የሚከሰቱ ናቸው” የሚል የኩነት መንስኤነት (event causality) እሳቤን የሚያመለክት ነው። በእርግጥ ይህ አይነቱ የመንስኤነት አረዳድ ሜካኒካዊ በሆነው ዓለም ውስጥ ትርጉም የሚሰጥበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ የፕላኔቶች እንቅስቃሴ፣ የወንዝ ጅረት፣ ኬሚካላዊ መብላላት... ወዘተ አይነት ኩነቶች ሜካኒካዊ በሆኑ ክስተቶች መንስኤነት የሚዘወሩ ይመስላሉ። እንዲህ አይነት የመንስኤነት አረዳድ ግን ትክክለኛውን የመንስኤ እና ውጤት (cause and effect) ባህሪን ሊያብራራ የሚችል አይሆንም።

ትክክለኛው የመንስኤነት ህግ (law of causality) ምንነት፣ “ሁሉም ኩነቶች ከኩነቶች ይመነጫሉ” የሚል የኩነት መንስኤነት ሳይሆን፤ “ሁሉም ድርጊቶች የአካላት ድርጊቶች ናቸው፣all actions are actions of entities” የሚል አሪስቶትላዊ የአካላት መንስኤነት (entity causality) ነው። የሁሉም አካላት ድርጊት የሚወስነው ደግሞ የአካላቱ ምንነት (identity) ወይም ተፈጥሮ ነው። አይን ራንድ፣ “ማንኛውም ነገር ወይም አካል ከተፈጥሮው ውጪ የሆነን ድርጊት ሊያከናውን አይችልም፤ ማንኛውም አካልም ተፈጥሮውን የሚቃረን ድርጊት ሊያከናውን አይችልም” በሚል ትገልፀዋለች የመንስኤነት ህግን። እንዲህ አይነቱ የመንስኤ-ውጤት (cause-effect) አረዳድን በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ውስጥ በተጨባጭ የምናስተውለው ነገር ነው። የብርቱካን ዛፍ የብርቱካን ፍሬ እንጂ አፕል ሲያፈራ፣ አህያ ሲያላዝን እንጂ ሲናገር፣ ውሃ ሲተንን ወይም ወደ በረዶ ሲቀየር እንጂ ወደ ወይን ሲቀየር አናይም አናስተውልም።

“ሁሉም ኩነቶች ከኩነቶች ይመነጫሉ” የሚለው የመንስኤነት ሞዴል ደግሞ ስህተት መሆኑን አሁንም ከዕለት ተዕለት ኑሮአችን በተጨባጭ ማስተዋል የምንችለው ነገር ነው። የሚሮጥ ነገር/አካል በሌለበት “ሩጫ” የሚባል ኩነት የለም፤ የሚናገር ነገር/አካል ሳይኖር “ንግግር” የሚባል ኩነት ሊኖር አይችልም። “ሀይሌ ገብረ ስላሴ እየሮጠ ነው” እንላለን እንጂ፣ “ሩጫው እየሮጠ ነው” ልንል አንችልም፣ከሚሮጠው አካል የተነጠለ “ሩጫ” የሚባል ድርጊት ወይም ኩነት ልናይ አንችልምና።

አሁን በክፍል አንድ የተመለከትነውን የሳም ሐሪስን (Sam Harris) መከራከሪያ እናስታውስ፣ “ማሰብ ዝም ብሎ የሚከሰት ኩነት ነው እንጂ የሐሳቦች አሳቢ ወይም አመንጪ የሚባል አካል የለም... ሐሳቦች እንዲሁ ይከሰታሉ እንጂ የሐሳቦቹን አሳቢ ብትፈልጉ አታገኙትም ” ይለናል።
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 6

እንግዲህ ሐሪስ፣ “ሐሳብ እንጂ አሳቢ የለም” እያለን ያለው፣ “ሩጫ እንጂ ሯጭ የለም”፣ “መትነን እንጂ የሚተን የለም”... ወዘተ እንደ ማለት ነው። የኩነት መንስኤነት መራራ ውድቀትም እዚህ ላይ ነው። አሪስቶል ከ 2400 አመታት በፊት በትክክል እንዳስተዋለው የህላዌ ተቀዳሚ ገፅታ ኩነቶች ሳይሆኑ አካላት ናቸውና። ይሄን የአሪስቶትልን ሐሳብ ለማብራራት አንድ በኩነት መንስኤነት ሞዴል አቀንቃኞች ዘንድ በተደጋጋሚ የሚነሳ ምሳሌ እንመልከት። አንድ የከረምቡላ ኳስ ሌላ የከረንቡላ ኳስን ስትገጭ፣ የተገጨችው ኳስ የምትንከባለለው የከረንቡላ ኳስ ስለሆነች እንጂ የኩነት መንስኤነት አቀንቃኞች እንደሚሉት ስለ ተገጨች አይደለም። የምትገጨዋ ኳስ የጥጥ ኳስ ብትሆን ኖሮ የከረንቡላ ኳስ ስለ ገጫት አትንከባለልም ነበር። ይልቅ የከረንቡላ ኳሷ የጥጥ ኳሷን ዳምጣት ነበር የምታልፈው። ትክክለኛው የመንስኤነት ህግ፣ “ሁሉም ድርጊቶች የአካላት ድርጊቶች ናቸው፤ የማንኛውም አካል ድርጊት ደግሞ በአካሉ ምንነት ወይም ተፈጥሮ የሚወሰን ነው” ማለት ይኼው ነው።

እንግዲህ በተወስኖታውያን መከራከሪያዎች ላይ እንዲህ የመሳሰሉ ጠንከር ያሉ ትችቶች የሚሰነዘሩ ቢሆንም ቅሉ፤ በክፍል አንድ እንደ ተመለከትነው ደግሞ ተወስኖታውያን በነፃ ፈቃድ አቀንቃኞች የነፃ ፈቃድ መገኛ ቦታ ሀልዮት ላይ የማያወላዳ ትችት መሰንዘር ችለዋል። እናስ እኛ ሰዎች ነፃ ፈቃድ አለን ወይስ የለንም? መገኛ ቦታውስ?

እስከ አሁን ከታዩት የነፃ ፈቃድ አቀንቃኞች መከራከሪያዎች ለየት ባለ መንገድ እነዚህን ጥያቄዎች በመመለስ የነፃ ፈቃድ ጉዳይን እልባት አስቀምጦለታል ብዬ የማስበውን የአይን ራንድ እይታን በመጨረሻው ክፍል በክፍል ሦስት እንመለከታለን።

ሰላም!

ብዙ ፍሬ ሐሳቦችን የተዋስኩባቸው ማጣቀሻዎች
1. Free will vs Determinism, Essay by Craig Biddle—The Objective Standard Substack
2. Volution as Cognitive Self-Regulation, Essay by Harry Binswanger in his Book Ayn Rand’s Philosophic Achievement
3. The Illusion of Determinism, Book by Edwin A Locke
4. Free Will, Book by Sam Harris

ተጨማሪ ማጣቀሻዎች
5. The Neural Basis of Free Will, Book by Peter Ulric Tse
6. Organisms, Agency and Evolution, Book by D M Walsh
7. Mind, Book by John Searle
8. Consciousness Explained, Book by Daniel Dennett
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 7

(መወድስ)
ለአፈር ጌጡ ንጉስ

ሲል አምላክ አሰፋ

ለአፈር ጌጡ ንጉስ

(መወድስ)

ሲል አምላክ አሰፋ

በአፈር የሚያጌጠው፥ ንጉሱ ቅዱሱ
መጋቢ በቁምጣው፥ ዳኛ በበርኖሱ
ቁጭ ብሎ ፈራጅ፥ ቁሞ ለመዋሱ፤
ትንግርት ነው እሱ!

ስልጡን የሚንቀው፥ከተሜ እሚያገለው ሰማይ እና መሬት፥ የሚያገለግለው ዝናብ ከደመና፥ በፀሎቱ አላቢ
ልቡን ወደ ፍቅር፥ ሽምጥ ጋላቢ አለቱን ቀራፂ፥ ብረቱን አንጣሪ ከሰው አልፎ ተርፎ ወፈ ሰማይ ጧሪ ሞግቶ እሚረታ፥ መክቶ እሚመታ
ማታ ማታ በሬ፥ ጧት ህልም የሚፈታ
ግሩም ነው የኔታ!

አርበኛ ነፍጥ አንጋች
እንደ ንብ፥ ማር አንጓች
ፈገግታው የለዛ፥ ሳቁ የምስራች
አንድ እጁ ከዳዊት፥ አንድ እጁ ከመውዜር ቁጣው እንደ ገብርኤል፥ ይቅርታው እንደ እግዜር አዛኝ እንደ ማርያም፥ ሩህሩህ ገራገር
በራሱ እጅ ቡጢ፥ ደረቱ እሚወገር
ድንቅ ነው ባ’ላገር!

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 9

ደግሞም እሚሳዝን
ዝንተ ዓለም፥ዘለዓለም
‘ሩር ነው
ጥንግ ነው
ገና መጫወቻ
ሁሉም ወደ ግቡ፥ የሚመታው በአቻ

ለዘንዶ ‘ራት ግብር፥ በኩር ልጁን ሰጥቶ በማይገባው ጉዳይ፥ ኖረ እንጅ ተከፍቶ እሱ ከአፈር ሌላ፥ አያውቅም ሰው ገፍቶ ይሔስ ያስተክዛል...

ሳይገደው ዋሽንቱ፥ ሳይነጥፍ ማሲንቆው ድምፁ ጠፍቶ ቀሪ፥ በዱር በሸለቆው ከሞፈር ከቀንበር ፥በዝቶበት ማነቆው የሆነውን ቢሆን...
ከእውነት አይሸሽም
ያልፋል እንጅ አይዋሽም
አፈር ጌጡ ንጉስ፥ ነው የመረሻ ሹም እንኳንስ በቁሙ፥ ሙቶ አይበላሽም!

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 10

የእኩልነት ቅዠት
(ግለሰባዊነት፣ ካፒታሊዝም እና የዘመናዊ ዲሞክራሲ ቅራኔዎች)

ዮዲት አማኑኤል



የእኩልነት ቅዠት
(ግለሰባዊነት፣ ካፒታሊዝም እና የዘመናዊ ዲሞክራሲ ቅራኔዎች)

“There is no God, but don’t tell my servant, lest he kill me.” — Voltaire
በአንድ ወቅት ፈረንሳዊው ፈላስፋ ፍራንኮይስ ማሪያ አሪዮት (ቮልቴር) ከአሳቢና አሰላሳይ ጓደኛው ቤይል ጋር ተቀምጠው እያወሩ ሳለ...

አሰላሳዩ እና ፈላስፋው እንግሊዛዊው ቤይል ለቮልቴር እንዲህ የሚል ጥያቄውን ወረወረለት፦

“በፈጣሪ የማያምኑ አላማኝ ሰዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ቢበዙ ጥሩ ይመስልሃል?” ቮልቴርም አሳቢ ጓደኛውን በጥልቀት ካየው በኋላ እንዲህ ብሎ ይመልስለታል።

“አዎ ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ። ነገር ግን እነዚህ በፈጣሪ የማያምኑ ሰዎች ከተቻለ ፈላስፋ መሆን አለባቸው። ከሰው ልጅ ውስጥ ደግሞ ጥቂቱ እንጂ አብዛኛው ፈላስፋ ሊሆን አይችልም። ፈላስፋ ካልሆኑ ደግሞ በአምላካቸው ማመን ይገባቸው ነበር። ካልሆነ በአላዋቂነታቸው ላይ አላማኝነታቸው ሲጨመር ታላቅ ጥፋት ይሆናል።”

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 12

ይህ አባባል በእውነት እና በማህበራዊ አስፈላጊነት መካከል ያለውን የማያቋርጥ ውጥረት እና፣ በሰዎች መሀከል ያለውን የአስተሳሰብ ልዩነት ይገልጻል። ቮልቴር እንዲህ ያሉ እውነታዎችን ሁሉም ሰው ሊረዳቸው የሚገቡ እውነታዎች እንዳልሆኑ፤ ይልቁንስ ብዙዎቹ የፈጠራ ትርክቶች ላይ ማመናቸው የተሻለ እንደሆነ ለመግለፅ የሞከረ ይመስላል። የተወሰኑ እምነቶች የሚጠበቁት እውነት ስለሆኑ ሳይሆን ጠቃሚ እንደሆኑ ስለሚታሰቡ ነው።

በዘመናዊው ዓለም ውስጥ፣ እንዲህ ካሉ እምነቶች አንዱ የሰው ልጅ እኩልነት ነው። የዲሞክራሲ ፅንሰ ሀሳብ “ሁሉም ግለሰቦች እኩል ናቸው” በሚል መርህ ላይ ቢገነባም፣ የሰው ተፈጥሮ እና ኢኮኖሚያዊ እውነታ ግን ሌላ ነገር ይጠቁማሉ። በዚህም ዘመናዊ ስልጣኔ በአንድ ተቃርኖ ላይ እንደተዋቀረ ያሳያል። በዲሞክራሲ አማካኝነት እኩልነትን በፖለቲካ ሊያረጋግጥ ሲሞክር፣ በግለሰባዊነት እና በካፒታሊዝም በኩል ደግሞ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ-ልቦናዊ ሁነቱ እኩል አለመሆንን ያሳያል።

አዳም ስሚዝ የገበያን ድብቅ አመክንዮ ከመተንተኑ ከረጅም ጊዜ በፊት፣ የሰው ልጅ ሕይወት ዝግ ባለ ኢ-እኩልነት ውስጥ ይኖር ነበር። ሰዎች ባላቸው አቅም፥ ክህሎትና ስነልቦና ይለያያሉ። ዕድልም በትውልድ መካከል እኩል ባልሆነ መንገድ ለአንዱ ስትቀርብ ከሌላው ትርቃለች። አንደኛው ሲያዝ ሌላው ይታዘዛል። ይሄ ሆነ ተብሎ በህግ የተቀረፀ ነገር ሳይሆን የተለያየ ችሎታ፣ ሁኔታዎች እና አጋጣሚዎች የሰሩት ስርአት ነው። ይህንን ለማረጋገጥ ምንም ዓይነት ንድፈ-ሃሳብ አያስፈልግም ነበር።

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 13



ሆኖም ግን በዚህ እኩልነት በሌለበት ዓለም ውስጥ አንድ አስደናቂ ነገር ተከሰተ፦ ልውውጥ! ገበሬው እህልን በመሳሪያዎች ለወጠ፤ ሱፍን በዳቦ ቀየረ፤ አንደኛው ባለው ነገር የሌለውን ነገር በመለወጥ መገበያየት ጀመረ።

ከባዮሎጂያዊ እና ስነ-ልቦናዊ እይታ አንጻር የሰው ልጆች ተመሳሳይ አይደሉም። በማሰብ ችሎታ፣ በፈጠራ፣ በምኞት፣ባላቸው እውቀት፣ በውሳኔ አሰጣጥ፣ ሀላፊነትን በመውሰድ እንዲሁም ባላቸው የሚና፣ ልዩነቶች በግለሰቦች መካከል በግልጽ ይታያሉ። እንደ ፍሬድሪክ ኒቼ ያሉ አሳቢዎች ይህንን እውነታ በማጉላት፣ የሰው ልጅ በተፈጥሮው ተዋረዳዊ መሆኑን እና ልዩ ችሎታ ያላቸው ግለሰቦች ከብዙሃኑ በላይ እንደሚወጡ ተከራክረዋል። ይህም የዲሞክራሲን የሞራል መሰረት ይፈታተናል።

ግለሰቦች በችሎታቸው እኩል ካልሆኑ፣ ውሳኔዎቻቸው ማህበረሰቡን በመቅረጽ ረገድ እንዴት እኩል ሊታዩ ይችላሉ?

የዲሞክራሲ ፅንሰ ሀሳብ ላይ ትልቅ ትችት ከሚሰነዝሩት ፈላስፎች አንዱ ፕሌቶ ነው።

“ዲሞክራሲ የተሻለ እውቀት በሌላቸው በብዙሀኑ ድምፅ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ወደ ስርዓት አልበኝነት እና አምባገነንነት ሊያመራ
ይችላል” ይላል። ይህም በቂ እውቀት የሌለው ህዝብ
የሚመራው ማህበረሰብ፣ በባለሙያ ካፒቴን ፋንታ
በተሳፋሪዎች እንደሚመራ መርከብ ነው በማለት
ይገልጸዋል። The republic በተሰኘው መፅሐፉ ላይም

“Democracy… is a charming form of gov-ernment, full of variety and disorder; and dispensing a sort of equality to equals and unequals alike.” ሲል ይተቻል።

Game of throne ላይ ታይሪዮን ላንስተር፣ ቫሪስ፣ ሰርሲ ላንስተር ይሄን ጉዳይ አንስተው ሲያወሩ እናያለን።

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 14

Tyrion Lannister:
“You think letting the people decide will bring justice? Their whims are louder than wisdom. Freedom without sense is cha-os.”

Varys:

“And yet, if we do not give them some voice, they will rise against us anyway. But their voice is often blind.”

Cersei Lannister:

“The strong must rule. Equality is a fantasy. Leave it to those with the eyes to see the truth.”

አሌክሲስ ደ ቶክቪል (Alexis de
Tocqueville): ዲሞክራሲ ወደ
“ብዙሀኑ አምባገነንነት” (Tyran-
ny of the majority) ሊያመራ
እንደሚችል ይናገራል። እኩልነት
ነፃነትን ከመፍጠር ይልቅ ገለልተኛ
አስተሳሰብን ሊገድብ ይችላል ይላል።
ኒቼ በበኩሉ እኩልነትን እንደ
“የሞራል ቅዠት” ይቆጥረዋል። “እኩልነት የሰውን ልጅ ታላቅ የመሆን ሀይል ያፍናል። እንዲሁም ተፈጥሯዊ የሰውን ልጅ አቅም ተዋረዳዊነት ይክዳል።” ሲል ተከራክሯል። ኒቼ On the Genealogy of Morality በሚለው መፅሃፉ እኩልነት የተፈጠረው ከ “ደካሞች” በላይ ያሉ ጠንካሮችን ለመቆጣጠር ነው። ሰዎች በተፈጥሮ እኩል አይደሉም፤ ኃይል፣ ጥበብ፣ ፈጠራ በሰዎች መካከል ልዩነቶች አሉ። ለእሱ የእኩልነት ቋንቋ እውነት ሳይሆን፣ በበጎነት ስም የተሸፈነ የባርነት ስነልቦና መሰረት ነው።

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 15





አዳም ስሚዝ በ The Wealth of Nations መጽሐፉ የኢኮኖሚ ሕይወት መርሆዎችን ሲያብራራ፣ በገበያ ውስጥ እኩልነትን አላገኘም። ይልቁንም ይበልጥ ተጨባጭ የሆነውን እውነታ ገለጠ። ግለሰቦች በግል ጥቅማቸው ተገፋፍተው፣ ሳያስቡት ሥርዓትን እንደሚፈጥሩ አሳየ። ነገር ግን ይህ ሥርዓት ሚዛናዊ
አይደለም። ንግድ ኢ-እኩልነትን አላጠፋም።
ይልቁንም በእሱ ላይ የተመሰረተ ነበር።

ይህ በአዳም ስሚዝ የተፃፈው (The Wealth of Na-
tions) በኢኮኖሚክስ ዘርፍ ቀዳሚና መሠረታዊ ሥራ
ሲሆን፣ ለቀደምት የኢኮኖሚክስ ትምህርት (classi-
cal economics) መሠረት የጣለ ነው። ስሚዝ በዚህ መጽሐፉ አገራት እንዴት ሀብት እንደሚያመነጩ፣ የገበያ፣ የሰው ሀይል እና የመንግሥት ሚና ምን እንደሆነ፣ እንዲሁም በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የሰዎችን ባሕርይ ይመረምራል።

በዚህ መጽሐፉ የሥራ ክፍፍል (Division of labor)
የምርታማነትን ብቃት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጨምር
ይከራከራል። ለምሳሌ፡ በአንድ የመርፌ ፋብሪካ ውስጥ
ሠራተኞች በተወሰነ የሥራ ዘርፍ ላይ ብቻ ካተኮሩ፣
እያንዳንዱ ሠራተኛ ብቻውን ከሚሠራው በበለጠ
በምርት ሂደት ውስጥ እያንዳንዱ ሰራተኛ ስራውን
ተከፋፍሎ ቢሰራ በተሻለ ሁኔታ በሺዎች የሚቆጠሩ
መርፌዎችን ማምረት ይቻላል ይላል። ይህም ልዩነትን
መሠረት ያደረገ የስራ ክፍፍል ነው።

ሰዎች በተፈጥሯቸው በግል ጥቅማቸው ተገፋፍተው ምርቶችንና አገልግሎቶችን እርስ በእርስ ይለዋወጣሉ። ይህም የልውውጥ መሠረት (Origin of exchange) እንደሆነ ያስረዳል።

ኢ-እኩልነት በተፈጥሮ መከሰቱ (Inequality emerges naturally) የተለያየ የክህሎት ደረጃ እና የምርታማነት ልዩነት መኖር፣ አንዳንዶች ከሌላው በበለጠ

እንዲያገኙ ያደርጋል ይላል። ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 16



ስሚዝ ተግባራዊ ኢኮኖሚክስን ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር ያዛምዳል፤ የግለሰቦች የራስ ጥቅም ፍላጎት ለማህበረሰቡ ብልጽግና አንቀሳቃሽ ኃይል መሆኑን ይገልጻል። ገበያው እኩል አይክስም፤ አንዱን ከአንዱ ይለያል፤ ይመርጣል፤ እንዲሁም ያጎላል። ባለሙያው ካልሰለጠነው በበለጠ ፍጥነት ከፍ ብሎ ሲታይ፣ መረጃ ያለው ካላዋቂው ሲቀድም፣ ዕድለኛ የሆኑት ጥቅማቸውን ከጥረታቸው በላይ ያሰፋሉ።

ግለሰብ ለራሱ ጥቅም የሚያደርጋቸው ነገሮች በተዘዋዋሪ ማህበረሰቡን ይጠቅማሉ። ለምሳሌ አንድ ግለሰብ ገንዘብ ለማግኘት ሲል ዳቦ ማምረት ቢጀምር፣ በአካባቢው ያሉት ሰዎች ደግሞ ይሄን ዳቦ ማግኘት ይችላሉ። ከራስ ጥቅም የሚነሳ ድርጊት ወደ ማህበረሰብ ጥቅም እንደሚሸጋገር አብራርቷል። በዚህም ሂደት ስሚዝ (Invisible hand) የሚለው ኢኮኖሚውን እየመራ የሰውን ልጅ ኢ-እኩልነት በሥርዓት ውስጥ ያጎላል ይላል። እዚህ ጋር ነው ውጥረት የሚፈጠረው የኢኮኖሚ ሕይወት የሰውን ልጅ ልዩነት ሲያጋልጥ፣ ፖለቲካዊ ሕይወት ደግሞ ራሱን ለመከላከል ለሰው ልጅ እኩልነት ሲከላከል እናየዋለን።

ዣን ዣክ ሩሶ Discourse on science and Art በሚለው ስራው የኢ-እኩልነት አይነቶችን ተፈጥሯዊ እና ተፈጥሯዊ ያልሆኑ ብሎ ይለያቸዋል። ተፈጥሯዊ ያልሆኑት ሊጠፉ እንደሚችሉ ታሳቢ ያደርጋል። የሰው ልጅ በሁለት መርሆች ይነሳሳል ይላል። ራስን በመጠበቅ (self-presentation) እና ሀዘኔታ (sympathy) ናቸው። ነገር ግን ሰው ከሌላው እንስሳ በተለየ ምሉዕነትን (per-fection) ይሻል። ሰዎች ከሌሎች ጋር በሚኖራቸው ማህበራዊ መስተጋብር እሱ ‘’አሞር ፕሮፕሬ’’ ብሎ ወደሚጠራው መርህ ይመራዋል። ይኸውም ሰዎች ራሳቸውን ከሌሎች ጋር እንዲያወዳድሩ እና በሌሎች
ሰዎች ላይ የበላይነት በማግኘት ደስታን ለማግኘት
እንዲሞክሩ ያደርጋቸዋል። የግል ሀብት እና የሀይል
ልዩነት ማህበረሰቡን ይከፋፍሉታል። ለሩሶ ተፈጥሯዊ
መበላለጥ በቁሳዊ ወይም አካላዊ ጥንካሬ ላይ የተገደበ
ነው።

ነገር ግን ከሚታዩ ልዩነቶች ሁሉ በታች መሠረታዊ አንድነት አለ የሚል ሀሳብ ያነሳል። እያንዳንዱ ግለሰብ

እኩል ግምት እንዲሰጠው የሚያስችል የሞራል እኩልነት ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 17

አለው። ዲሞክራሲ የተገነባውም በዚህ እኩልነት ይገባኛል ጥያቄ ላይ ነው። እኛ በችሎታ እኩል ስለሆንን ሳይሆን፣ በክብር እኩል እንደሆንን ተደርገን መታየት ስላለብን ነው። ሩሶ ተፈጥሯዊ የሆነውን ልዩነት እና ኢ-እኩልነት ባይክድም The social contact በተሰኘው ዝነኛው ስራው ላይ በማኅበራዊ ውል ውስጥ የፖለቲካ እኩልነት የሕጋዊ መንግሥት መሠረት እንደሆነ አፅንዖት ይሰጣል። እውነተኛ ነፃነት የሚመነጨው ሁሉም ግለሰቦች የሚተዳደሩባቸውን ሕጎች በማውጣት በእኩልነት ሲሳተፉ ነው። የፖለቲካ ተቋማት ከማኅበራዊ ጥቅሞች የሚመነጨውን አለመመጣጠን መቀነስ አለባቸው፣ ይህም ዜጎች በሕግ ሥር በእኩልነት እንዲታዩ ማድረግ ነው ይላል።

ሆኖም ቅራኔው የሚፈታ አይደለም። በገበያ ቦታ፣ ኢ-እኩልነት ተግባራዊ ጠቀሜታ አለው። በፖለቲካው ደግሞ እኩልነት መሠረታዊ ነው። ገበያው ትክክለኛ ተፈጥሯችንን ሲገልጥ ፖለቲካው ደግሞ ምን መስለን መታየት እንዳለብን ያዝዛል።

በተቃራኒው ካርል ማርክስ ኢ-እኩልነትን የካፒታሊዝም እውነታ አድርጎ ይቀበለዋል። በተፈጥሮ የሰው ልጆች እኩል አይደሉም ከሚለው ይልቅ የካፒታሊዝም ስርአት እና የማህበረሰብ የመደብ ስርዓት የወለደው እንደሆነ ያምናል። ስሚዝ ይህን ሥርዓትን ባየበት ቦታ፣ ማርክስ እንደ ብዝበዛ ተመልክቶታቷል። ገበያው ልዩነትን ባነገሰበት ቦታ፣ ማርክስ ማስተካከያ እንዲደረግ ጠይቋል። ሁለቱ ትችቶች አቅጣጫቸው ተቃራኒ ቢሆንም፣ በአንድ ነገር ላይ ግን ይስማማሉ። እኩልነት በተግባራዊ ተሞክሮ ውስጥ የለም።

ታድያ በዕለት ተዕለት ህይወታችን እንኳ እኩልነት ከሀሳብ የዘለለ ሀቅ እንዳልሆነ እያየን ማህበረሰቦች ለምን በእኩልነት ላይ ሊፀኑ ቻሉ። መልሱ ያለው በእውነት ውስጥ ሳይሆን ህልውናን ለማስቀጠል በሚደረግ ትግል ሊሆን ይችላል። በእኩልነት ላይ የተመሰረተ እምነት ከሌለ ኃይል ብቻ ዋጋን የሚወስንበት፣ እና የደረጃ ልዩነት ወደ ዘላቂነት የሚቀየርበት ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ የሚል ስጋት አለ።

የዘመኑ ሰው በሁለትዮሽ የተቃርኖ ዓለም ውስጥ ማለትም በእውነትና በአስፈላጊነት መካከል ባለው ደካማ ሚዛን ላይ ቆሟል። በፖለቲካ ውስጥ የእኩልነትን በመብቶች፣

በሕጎች እና በዲሞክራሲያዊ ድምፅ ሊያረጋግጥ ይሞክራል። በኢኮኖሚው መስክ ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 18

ደግሞ በውድድር፣ በሽልማት እና በውጤት አማካኝነት ከኢ-እኩልነት ጋር ይጋፈጣል። አንዱን ያምናል፣ ሌላኛውን ይኖረዋል።

ስለሆነም እኩልነት እውነታ ሳይሆን በእውነታው ላይ የተቀመጠ ገደብ ነው። ጠንካራውን የሚገታ፣ ደካማውን የሚጠብቅ እና እኩል ባልሆኑ ሰዎች መካከል አብሮ መኖርን እንዲቻል የሚያደርግ መርህ ተደርጎ ይታሰባል።

በዚህ ረገድ የእኩልነት ፅንሰ ሀሳብ የቮልቴርን አምላክ ይመስላል። ኃይሉ ያለው በተጨባጭ እርግጠኝነት ላይ ሳይሆን፣ በማህበራዊ አስፈላጊነቱ ላይ ነው። ቮልቴር እንዲህ ይላል።

‘’If there were no God, it would be necessary to invent him.”

እኩልነት ባይኖር እንኳን የእኩልነትን ፅነሰ ሀሳብ መፍጠር እና ሰዎች በሀሳብ እኩል እንደሆኑ ማሳመን አስፈላጊው ነገር ይሆናል። “እኩልነት የሰው ልጅ ተፈጥሮ መሠረት ሳይሆን፣ የሰው ልጅ አብሮ ለመኖር በምናብ የገነባው ቅዠት ነው። ምን አልባትም አስፈላጊ አሊያም አደንዛዥ መርህ ነው።

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 19

ዘርዓያዕቆብ የፍልስፍና ት/ቤት ዘንድሮ ፒያሳ በሚገኘው ካቴድራል ት/ቤት በየሁለት ሳምንቱ ቅዳሜ የሚካሄድ “የበጋ ሌክቸሮች” መርሐ ግብር እያካሄደ ነው። እስከ ግንቦት መጨረሻም ይቆያል።

የበጋ ሌክቸሮች መርሐ ግብር ከፍልስፍና ጋር በቀጥታ ከሚገናኙ የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች በተጨማሪ፤ በማንኛውም የመደበኛ ትምህርት ኮርስ አሰጣጥ ላይ ተገቢ ጊዜ ተመድቦላቸው የማይዳሰሱ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ-ኢኮኖሚ፣ የአርት…ወዘተ ርእሰ ጉዳዮችንም በፍልስፍናዊ አውድ የሚዳሰሱበት መርሐ ግብር ነው። በዚህም የበጋ ሌክቸሮች መርሐ ግብር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ነው።

ለምሳሌ ያክል:-

፩. በየተሰማራንበት የሙያ/የስራ መስክ ውስጥ ፍልስፍናዊ አስተሳሰብ የሚኖረውን ድርሻ የምንገነዘብበት ነው።

፪. ተማሪዎች ለመመረቂያ ፅሑፍ የሚሆናቸውን የተለያዩ የሐሳብ ጭብጦች የሚገበዩበት ነው።

፫. የአርት እና የሚድያና መዝናኛ (ደራሲዎች፣ ገጣሚዎች፣ ሰዓሊዎች፣ ጋዜጠኞች፣ የፊልምና የትያትር ባለሙያዎች...) ሰዎች ላሉበት የሙያ መስክ የሚመጥኑ ርእሰ ጉዳዮችን በፍልስፍናዊ መነፅር (ሰፊ በሆነ የህይወት እና የህላዌ

ምልከታ) መዳኘት እንዲችሉ የሚያግዛቸው ነው።

፬. አስተማሪዎች ድግግሞሽ ከበዛበት የኮርስ አሰጣጥ ሂደት ወጥተው፤ ተማሪዎቻቸውን ማሰብ በሚያስችላቸው ፅንሰሐሳባዊ ሂደት እንዴት ማስተማር እንደሚችሉ የሚጠቁማቸውን ፍልስፍናዊ የማሰብ ክህሎት የሚገበዩበት ነው። ...የበጋ መርሐ ግብሩ ሁሉም በነፃ የሚሳተፍበት ፕሮግራም ነው።

ቦታ: ፒያሳ በሚገኘው ካቴድራል ት/ቤት 2ኛ ፎቅ

ዘርዓያዕቆብ የፍልስፍና ት/ቤት

የተሰጡ ስልጠናዎች በጥቂቱ

ቴሌግራም- ደቂቀ_ዘርዓያዕቆብ (https://t.me/joinchat/fpCrKPBnBjE1MjI0)

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 20



ሞሲሳ ዳምሴ (ዶ/ር)

ሶስተኛው አወዳደቅ

ዝግም ያለ ቀን ነው። የእኔን ፊት የሚመሰል የሐምሌ ደመና እንደአንዳች ነገር ከላዬ ይከብደኛል። ቀና ብዬ አየሁት። እንደሁልጊዜው ሁሉ ቀና ብዬ ባየሁት ቁጥር፣ መንታዬ የሚመስለኝን ጥቁር ደመና ያዘቀዘቀውን ሰማይ አወራሁት።

ፊትህ ለምን ይጠቁራል? ዛሬ ደግሞ በማን አዘንህ? ?በማን ተከፋህ? በማንስ ላይ ትቆጣለህ? ይህ ፊት፣ የእኔ ህሊና፣ የአግዜር ፊት ይሆን? አዬ ጉድ ደግሞ በማን ላይ ታጉረመርም ይዘሃል? ሆዴ አብሮ ይላወስ ጀመር። ባካናው ልቤ እንደካብ ይፈርሳል። ነጎድጓዱ ሰማዩን እያረሰ ያልፋል። ጠንከር ብሎ የጀመረው ካፊያ ቀስበቀስ እየበረታ ዶፍ ዝናብ መዝነብ ጀመረ። የሐምሌ ጭቃ እግሬን ይዞኛል።

ዛሬም ጥላ አልያዝኩም። እንደሁልጊዜው ይዝነብብኝ፤ ይውጣለት ብዬ ገብቼበታለሁ። አብረን እናነባለን። ጓደኛዬ ባህራን ቤት እየሄድኩ መንገድ ላይ ነኝ። ሰፈራቸው አስፓልትም ሆነ የኮብል መንገድ ስላልገባለት ጭቃው ለመራመድ ያዳግታል። በትግል ደረስኩ። ዝናቡ በርትቶ ኖሮ ዶፍ እየጣለ ነው። በፍቅር እወደው የነበር ዝናብ ያስፈራኝ ጀመር። ከወትሮው ለየት ይላል። ሰማዩ ደጋግሞ ያጉረመርማል። ነጎድጓዱ የሚያስፈራ መብረቅ ጅራቱን ያወናጭፋል። እንደምንም እየተጣደፍኩ የባህራን በር ጋር ደረስኩ። የግቢያቸው በር ታዛ ሰፊ ስለነበር በበቂ ሁኔታ አስጠለለኝ። ቀና ብዬ ባካኙ ልቤን አየሁት። አልወጣለትም መሰል ጥቁር ደመናውን እንደተከናነበ ነው። ሃዘኑ ቁጣ ሆኗል። ሆዴ ተረበሸ። ፈጠን ብዬ የባህራንን በር አንኳኳሁ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ባህራን ሰፋ ያለ

ሶስተኛው አወዳደቅ

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 22

ድባብ ዣንጥላ ይዞ እየሮጠ መጣ። በመምጣቴ ተገርሞ እንደ ታቦት ሸኚ ቤታቸው በረንዳ ላይ ስንደርስ ቆምን።

“እንዴት በዚህ ዝናብ መጣህ?” አለኝ ጥላውን አራግፎ በረንዳው ላይ እያስቀመጠ

“ዝናቡ ተመችቶኝ ነበር። መንገድ ላይ ስደርስ በረታብኝ።
የዛሬው ትንሽ ለየት ይላል።”

“የአንተ እና የዝናብ ነገር”

“ዛሬ ገብርኤል አልሄድክም? የሐምሌ ገብርኤል የአመቱ
ንግስ መስሎኝ።”

“ሄጄ ነበር። ዶፉን አልቻልነውም። ሰማይ የተከፈተ
ነበር የሚመስለው…ዝናብ በረከትም ቁጣም ሊሆን
ይችላል። የዛሬው ግን ተለየ…። ቅዳሴ ሳያልቅ አያቴን
እንዳይከብዳት ቶሎ ይዤአት መጣሁ…።”

“አዎን! ይሄስ ከቁጣም በላይ ነው… በጣም ነው ያስደነገጠኝ…ሊያፀዳን አስቦ እንዳይሆን?”

“ኃጥያታችን በዝቷል። ቁጣ ነው። በዚህ ሰዓት አይደለደም ዶፍ እሳት ቢዘንብ አትገረም።”

“የኖህ ዘመን ኃጥያተኞች ላይ እንደርሳለን ብለህ ነው? እንደው ሊያጠፋን ካሰበ ራሱ መርከብ አዘጋጅ የሚል መልዕክት ሊደርስህ ይችላል። እንዳንተ ያለ ያገኝ ይሆን? ታዲያ ጥንድ ጥንዱን ስታስገቢ እኔን ከመክሊት ጋር እ…።”

“አትቀልድ ባክህ። እግዜር እኮ ባንድም በሌላ ያስጠነቅቀናል። ነቅቶ መመለስ የእኛ ፋንታ ነው። እኔ ግን የአንተ ነገር ያሳስበኛል። በእምነት እና በእግዜር ህልውና ላይ ያለህ አመለካከት እንዲህ መለወጡ…።ወደ ክህደት መስመር ማሽቆልቆልህ…የማላውቀው ሙሴ ነው እኮ የሆነከው።”

“አያሳስብህ እምነትም ሆነ እግዜር ከልቤ የማይጠፉ ጥያቄዎች ናቸው...። ግን ጥያቄዎቼ ናቸው።”

“እንዴት ማለት?”
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 23

“አማኝ አይደለሁም፤ የእግዜር ህልውናም ያጠራጥረኛል። ግን ስለ እምነትም ሆነ ስለ እግዜር እጠይቃለው አነባለሁ።”

“እና ዘንድሮም እግዜር የለም እያልክ ነው?…ሎቱ ስብሃት!”

“ለእኔ አዎ። ህሊና ነው እግዜር። ባህራን በዚህ ወሬ ጊዜ ባናባክንስ? ተማምነን አናውቅም እኮ። መጨረሻው ጭቅጭቅ ነው።”

“አዎ የማይሆን ወሬ ነው። ይልቅ አደገኛ መብረቅ ሲወድቅ ሰምተሃል? ቤተ ክርስትያኑ ጀርባ ሳይወድቅ አይቀርም ይላሉ።”

“ተው ባክህ ከየት ሰማህ?”

“እናቴ በዛ ስታልፍ ከሰው ሰማች።”

“ማን ላይ ወደቀ?”

“እንዲሁ ባዶ ሜዳ ላይ አሉ”

“እንዲሁ ባዶ ሜዳ ላይ?”

“አዎ”

“አልተያዘም?”

“እንዴት አልተያዘም?”

“መብረቅ ተይዞ በሳጥን ተደርጎ ይሸጣል ሲባል አለሰማህም?”

ከት ብሎ ሳቀ

“አልተያዘም”

“ለምን ሄደን አናየውም?”

ዝናቡ ጋብ እስኪል በረንዳ ላይ ቁጭ ብለን የባጥ የቆጡን ስንዘባርቅ ቆየን።
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 24

ባህራን የምወደው ጓደኛዬ ነው። ከ አንደኛ ክፍል ጀምሮ አብሮኝ የተማረ ውድ ወዳጅ። አሁን የ17 አመት አፍላ ሆነን መንገዳችን ቢለያይም በጣም እንዋደዳለን። ባህራን ጠንካራ የእምነት ሰው ነው። ዝናቡ ፈፅሞ እስኪያቆም መታገስ ስላቃተን ያንን ድባብ ዣንጥላ ይዘን ወደ ሜዳው አመራን።

ዝናቡን ሽሽት በየገዛ መርከቡ የመሸገው ምዕመን ተመልሶ አልወጣም። ቤተክርስትያኑ ጭር ብሏል። በቤተ ክርስትያኑ የምዕራብ በር በኩል በግቢው በስተ ጀርባ አጥር ዞርን። ወለል ካለው ሜዳ ላይ ጉድባ የተማሰበት ቦታን አየን። መብረቁ ምን አይነት ጉድባ እንደማሰ ለማየት እና ወሬ ለማዳረስ እየቸኮልን ወደ ጉድጓዱ ተጠጋን። ከዚህ በኋላ ያጋጠመን ግን ለማመን የሚያስቸግር ነበር።

በእጆቹ የጭቃ ድቡልቡል ኳሶችን እየሰራ ያስቀምጣል። ያስቀመጣቸውን ኳሶች አንድ በአንድ ያፈርሳል። በእያንዳንዱ የመስራት እና የማፍረስ አፍታ ቀና ብሎ ሰማዩን ይመለከታል። ዓይኖቹን ቀና ሲያደርግ...ዓይኖቹ ትላልቅ ናቸው። የታጠቡ የወንዝ አለት ይመስላሉ። እንደ ጨረቃ ደመቅ ያሉ፥ በነጭ ሰማይ ላይ የተቀመጡ ጥቋቁር ዛጎሎች ናቸው። አፍንጫው የተንሰለከከ፣ እንደ ሸንበቆ ቀጥ ብሎ የሚወርድ ነው። ከናፍሮቹ የተመጠኑ ናቸው። ፊቱ የደስ ደስ ያለው ጠይም ዳማ ነው። እንዲያው በደፈናው መልኩ ፀዓዳ ነው። መላ ሰውነቱ በጭቃ ላቁጧል። ከላዩ ልዩ መዓዛ ይነሳል። ሁልግዜ ባህራንን ከቅዳሴ መልስ ሳገኘው የሚሸተውን የከርቤ እና የእጣን ጠረን ይመስላል። ይህ ጠረን ግን ከዚያም ይልቃል። ዓይናችንን ማመን አቅቶን ፈዘን ቆምን። ባህራን በድንጋጤ አፉን ከፍቶ ከጉድባው አፋፍ ላይ ቁልቁል ይመለከታል።

“ባህራን ምንድነው?” በሹክሹክታ ጠየኩት።

“እንጃ እኔም አላውቅም” ባህራን ግራ ተጋብቷዋል።

“ክንፍ አለው” አልኩት።

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 25

ክንፎቹ ከሚያብቀርቅ አልማዝ የተሰሩ ይመስላሉ። ግዙፍ ናቸው። ጭቃው ላይ ዘርገፍ ብለው ተዘርግተዋል።

“አየሁት” አለኝ

“መልዐክ ይመስላል።”

“ነው” አለኝ በቀዘቀዘ ድምፅ።
“እንዴት አወቅህ?”

“እንዲሁ።”

“እንዴ መላዕክት ረቂቅ ናቸው አይታዩም ያልከኝ አንተው አይደለህ?” ስለ መላዕክት የነገረኝን አስታወስኩት። ከእሳት እና ከነፋስ የተፈጠሩ የማይመገቡ የማይራቡ ረቂቅ ፍጥረታት እንደሆኑ ነግሮኛል። ያን ጊዜ “ማን አይቷዋቸው እንዲህ ናቸው ብሎ ሳላቸው?” ብዬ ጠይቄው ነበር። የሰጠኝ መልስ አልረሳውም። “ፈጣሪንስ ማን አይቶት ሳለ? ሁሉም ነገር ለአእምሮ እንዲመች ነው።” ነበር ያለኝ።

ዛሬ ግን ለጠየኩት ጥያቄ መልስ አልሰጠኝም።

ባህራን በደመ ነፍሱ እያወራ መሰለኝ።

መልዐክ የሚመስለው ፍጡር ቀና ብሎ ተመለከተን።
አስተያየቱ ውስጥ ድረስ ይሰማል።ተመልሶ አጎነበሰ
እና የሰራትን አንድ ድብልብል ጭቃ አፈረሳት።
ልቤ ደነገጠ። ሆዴ ተላወሰ። የፈረሰችውን የጭቃ
ድብልብል አተኩሬ ተመለከትኳት። የወደቀችውን
ፍራሽ ወደ እኔ ታፈጣለች። አሳዘነኝ።

“ስለ እኔ እየተነጋገራችሁ ነው? በምታውቁኝ እና ለአእምሮአችሁ ቅርብ በሆነ መልክ መጣሁ። እናንተው በሳላችሁኝ መልክ።”

ዝናቡ ቆሟል። ከወዲያ ማዶ የሰዎች ድምፅ ይሰማል። ወደ ቤተ ክርስትያኑ ቅጥር የሚገቡ ሰዎች ከጀርባ የምናየውን ጉድ ያዩ የሰሙ አይመስለኝም።

The Wounded Angel, Hugo Simberg, 1903

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 26

“ምነው ፈራችሁ??” አለን ድምፁ ቢደክምም እንደ በገና የረጋ እና ግርማ ያለው ነው።

ድንጋጤው ገና ከልባችን አልወረደም ነበር። እንደውም ድምፁን ስንሰማ አየለብን። መልስ አልሰጠነውም። የምናየውን በማመን እና በመጠራጠር መካከል ልባችን ይዋልላል።

“ማየት ማመን ብቻ እንዳይመስላችሁ፣ ለጥርጣሬ ይጋብዛል። በልባችሁ እምነት ያመናችሁትን አይታችሁ ሊያስክዳችሁ ይችላል። ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው ተብላችሁም ተብለንም ነበር። ስናይ እምነታችን ስለሚሸረሸር ይሆን? ወይስ እንደ ቶማስ ካላየን አናምንም ብለን እንዳንታበይ? እኔ እና እናንተ በፊት በመንፈስ እና በእምነት የምንተዋወቅ ምስጢረኞች ነበርን። አሁንስ?”

ተገትረን ቀረን። መልስ የመስጠት አቅም አልነበረንም። እርጋታው ግን ድንጋጤያችንን አለዝቦታል። ባህራን ለማልቀስ ቃጥቶታል። ይህን ፊት አውቀዋለሁ።

“አትሸበሩ! ባላችሁበት ረግታችሁ ተቀመጡ።”

ባህራን ከጉድባው አፋፍ ላይ ቁጢጥ አለ። ተከትዬው ተቀመጥኩ።

“የልባችሁን ሀሳብ መረዳት አልችልም። ነገር ግን ከሁኔታችሁ እና ከፊት ገፃችሁ በድንጋጤ፣ በጥርጣሬ እና በመደነቅ መካከል መሆናችሁን እረዳለሁ።”

“ምን አይነት ተአምር ነው?” አለ ባህራን አፉን በአጁ ጭኖ እያጉተመተመ። የሰማው አልመሰለውም

“የምትመለከቱት ተአምር አይደለም። ከአእምሯችሁ በላይ ሆኖ ይሆናል። ግን ተአምር አይደለም።”

“ይህ ተአምር ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል? ረቂቁ ፍጥረት ግዘፍ ነስቶ ወድቆ ተመለከትን።” አሁንም ለራሱ ከእራሱ ጋር እያወራ።

“ከአእምሮ በላይ ሆኖባችሁ ይሆናል። ችሎታችሁ፣ አቅማችሁ እና ክብራችሁ ከልዕልና ወርዶ ስላገኛችሁት ነው። ያጣውን የሚያውቀው ኖሮት ያየው አዳም ብቻ ነው።”

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 27

“አንተስ ያጣኸው ምንድነው?” ብዬ ጠየቅሁት ስፈራ ስቸር

“ያጣሁት ካገኘሁት አይልቅም።”

“እዚህ ከእኛ ዘንድ ምን አግኝተሀል?” ደፈር ብዬ ጠየቅሁት

“ልክ እንዳንተ ልክ እንዳሁኑ የመጠየቅ እና የመመርመር ፀጋ።”

“ግን መመርመር እና መጠየቅ የመካድ እርሾ አይሆንም?” ሁልጊዜ ባህራን የሚለኝን ነገር ነበር። ዛሬ ጠያቂው እኔ ስሆን ገርሞት ይሆናል።

“የማወቅ እርሾ ነው።”

“ሰማይ ቤት እንዴት ይሆን?” ሁሉንም ነገር ያማወቅ ጉጉት አድሮብኛል። በግማሽ ልቤ ባህራም ምን እያሰበ ነው የሚለውን እያሰብኩ።

“ከእምነት ውጭ ምንም የለም። ለእናንተ ምድር መቆያችሁ እንደሆነች ለእኛም ራማ እንዲሁ ነች። ሰማይ ቤት እና ፈጣሪ እምነታችን ናቸው። እንደናንተው ካላየሁ አላምንም እስክንል፣ ወይም አይተን ሳናይ አምነን ያጠበቅነው እስኪላላ።”

ከድንጋጤያችን ጋብ ብለናለን። ሳናስበው እንደ ቅርብ ወዳጅ መጨዋወት ጀምረናል። ይህ መልዐክ ያነበብኳቸው ታላላቅ ፈላስፋ መካከል አንዱን መሰለኝ። ሰርቶ ከሚያፈራርሳቸው የጭቃ ድቡልቡሎች ሁለት ቀርተዋል። አንዱዋን ደበስበስ ያደርጋታል። እንዳያፈርሳት ልቤ ሰጋ። በእምነት እና በመለኮታዊ ጉዳዮች ላይ አፍላዊ ትችት እና ምክንያታዊ ጥያቄዎች ቢኖሩኝም ዛሬ ልቤ ተፈትኗል። ጭላንጭልም ቢሆን የእምነት ቅሪት እንዳለኝ ተገነዘብኩ። ነገር ግን ሌሎች ካለማመን ወደ ማመን የመጡበት የተአምር እና የመገለጥ መንገድ አለመሆኑ፣ መሀል አካፋይ ላይ አስቀርቶኛል። እንደ ሳኦል በደማስቆ መንገድ የወረደ መብረቅ እና የተናገረኝ ድምፅ አልነበረም። ለባህራንም ከማይደራደርበት እምነቱ በስንዝርም ቢሆን ወደ መጠይቅ መንገድ የሚወስድ ክስተት እንደሆነ አልጠራጠርም። የጭቃ ኳሶቹን ለምን እንደሰራቸው አልገባኝም ነበር። እንደ ልጅ እየተጫወተ ይሆን አልል ነገር ከእርሱ የሚጠበቅ ነገር አይደለም። ታዲያ ለምን...?

“እንዴት መጣህ?” እንዴት ወደቅህ ብዬ የመጠየቅ ድፍረት አልነበረኝም።

“አምፀሃል በሚል ክስ”
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 28

“በማን ላይ?”

“በፈጣሪ ላይ”

“አምፀሃል?” አልኩት

“አላመፅኩም”

“እና?”

“የፈጣሪን ህልውና ግን እመረምር ነበር”

“በክህደት ነዋ የተባረርከው? የሳጥናኤል መንገድ ነው።” አለ ባህራን ኃይለ ቃል በተሞላበት ንግግር።

“ከነበርኩበት ከራማ በአመፅ ክስ ያባረሩኝ መላዕክት ያሉኝ ልክ አሁን እንዳልከው ነበር። ጥያቄዎቼን የመስማትም ሆነ በምክንያት የመነጋገር ፍላጎት አልነበራቸውም። የማንንም እምነት እና ነፃነት አልተጋፋሁም ነበር። ብቸኛ ነበርኩ። የእለት ተልዕኮዬን እወጣ ነበር። ግን ሁልጊዜ ጥያቄ ነበረኝ። ውጣም ተበዬ ተግዤ ስወረወር ቃል ሳልተነፍስ ተቀብዬ መጣሁ። ባህራን እንዳንተ ያለ እምነት አለኝ። ግን እንዳንተ ያለ በነፃነት አንተ መካድ ያልከውን የመጠየቅ ጸጋ አልነበረኝም። የወደኩት የአዳምን ሆነ የሳጥናኤልን አወዳደቅ አይደለም። ሳጥናኤል እኔ ፈጠርኩ በሚል ኩሸት እና ማታለል ሲወድቅ እኔ በዚያ ነበርኩ። እርሱ ግን ከእርሱ በላይ ማን እንዳለ አላወቀም ነበር። እኛም እንዲሁ።

አዳም ከገነት ተባሮ ሲወጣ የገነትን በር ለመጨረሻ ጊዜ ጀርባው ላይ የዘጋሁት እኔው ነበርኩ። አዳምም ከሳጥናኤል በተሻለ ከበላዩ አምላክ እንዳለ ቀድሞ ቢያውቅም የስልጣን እና የአምላክነት ፍላጎት ከምድር ጣለው። እኔስ? መመርመር መጠየቅ። ይህስ ሶስተኛው ይሆናል። እንደ ወንድሜ ሳጥናኤል ባልዋሽ እና ባልክድ እንደ ዘመዴ አዳም አምላክነት ባልመኝም”

ይህን ከተናገረ ወዲህ አንድ ጊዜ ወደ ሰማይ አንጋጠጠ እና ተመለከተ። የመጣበትን ረጅሙን ጉዞውን የሚያሰላስል ይመስላል። ሰዓቱ ረፍዷል። ቀኑ የንግስ በዓል ስለነበረ ቀደም ብሎ የጀመረው የሰርክ መርሐ ግብር ወደ ጆሮአችን ገባ። የደብሩ መምሕር ስብከት ከቤተ ክርስትያኑ ቅጥር ግቢ ይሰማል። ምዕመኑ በእልልታ እና በጭብጨባ ያጅባል።
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 29

ወደ ጭብጨባው እና እልልታው አቅጣጫ ተመልክቶ...

“ይህ እምነት ነው። ነገር ግን እዚህ መካከል በአርምሞ የተቀመጠ ጠያቂ አእምሮ አይጠፋም። ራሱን ቢገልጥ ከዚህ የእምነት ጉባኤ ይሰደዳል። ይህ ነበር የሆነው።”

“ንግግርህ እና ሀሳብህ ከእግዜር መልዐክ የሚወጣ አይመስልም።” አለ ባህራን

“አዎ። የመጣሁበትም እንዲህ አልነበረም። አሁን ላይ በሁለታችሁ ሀሳብ የሚዋልል ልብ ነኝ።”

በባህራን ጠነካራ እምነት እና እኔ ሙሴ በፈጣሪ ላይ ባለኝ ጥርጣሬ መካከል እንደሆነ የገባኝ ቆይቶ ነው።

“አሁን ሁለታችሁም ጋር ያለውን ፀጋ የተጋራኋችሁ ነፃ ፍጥረት ነኝ።”

“ነፃ ፍቃድ አለን? እጣ ፈንታችን ተፅፏል?”

“እግዜር ህሊናችሁ ምን ይላችኋል? እርሱን ስሙት።”

ለረጅም ሰዓት በአእምሮዬ ሲመላለስ የነበረ ጥያቄ ለመጠየቅ ሳመነታ ቆየሁ። ምናልባት አይቶትም ከሆነ እንዲያስረዳን እና በምስል እንዲከስትልን በጣም ጓጓሁ። ነገር ግን በድፍረት ለመጠየቅ ወኔውን አጥቼ ተውኩት። ምናልባትም ባህራን እንደ እኔ እያሰበ ይሆን? ብዙ ግዜ ከባህራን ጋር የተከራከርንበት ጉዳይ ነበር።

“ምን ልጠይቀኝ ነበር?” አለኝ በልብ የወጠንኩትን በጆሮ የሰማ መሰለኝ

“ፈጣሪ አለ?”

“ወደ እናንተ ያመጣኝ የመጨረሻ የመውደቄ ምክንያት ምን ይመስልሀል?”አለኝ።

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 30

ነቢል አዱኛ

ቋም አናወርስም



ቂም አናወርስም
Intercontinental ን እስካላየሁ የማልረጋጋበት ካዛንቺስ ላይ ቆሜያለሁ። አንድም የማስታውሰው ቦታ የለኝም። አንድ መንደር ሙሉ ይወድማል? በእንቅልፍ 309 ዓመታቸውን እንደተቀሙት አስሀቡል ከህፍ1

ኾነናል፤ የእኛ
ግን በቁማችን ነው። ትናንቱን የተቀማ ዛሬውን ከየት ያመጣል? እነሱ ሰባት ኾነው በጋራ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ስድሳ ሦስት ዓመት አጡ። እኛ ሦስት መቶ ሳያስፈልገን በጥቂት ሳምንታት የኖርንበት አካባቢ ባዕድ ኾነብን። የማናውቀው የፖላንድ ጎዳና ላይ ያለን ይመስል...። የሰባቱ ስምንተኛቸው ውሻ ነበር። ያልተለያቸው ታማኛቸው። እኛም ታማኝ የኾንለትና የኾነልን Art የተባለ ውሻ ጋር እንኖራለን። ከሰባቱ አንዱ ከዚያ ኹሉ መተኛት መኻል በዕንቅልፍ ልቡ ነቅቶ ውሻውን ወደራሱ ስቦ አቅፎ አልተኛም? ልክ እንደዚያ...።

ወደ መንደራቸው ሲመለሱ ውሃ ያወጡበት ጉድጓድ ፎቅ ኾኖ ሲያገኙ ቀዝቃዛ ላብ በደረታቸው መኻል አልወረደም? እዚህ ካዛንቺስ ማኪያቶ የጠጣሁበት ካፌ የቱ ጋር ነው የነበረው? ይቅር እሱ... የደራሲው ቤት ምን ጋር ነበር? እዚያች ወንበሩ ላይ ኾኖ ዐይቻቸው የማላውቃቸው መጻሕፍት ከጀርባው ተደርድረው ፈገግ የሚልባት ቤት?

እንደ ገብርዬ ፊት በምታሳሳው እጁ የሚገልጣት አልጋው የነበረበት ቦታ? ከተጠረዘ ወረቀት ውጭ ሕልም የሚመስል ከጓዶቹ ጋር ሲያወራ የምናደምጥበት?

አቃፊ-ደጋፊ የሌላቸው እንዳስለመዳቸው ጉርሳቸውን እንዲመፀውታቸው የሚመጡበት?

በልባችን ወይም በአዕምሯችን ብቻ ያለች ሃገር ከዕውነታው ጋር ሳትስማማ ስትቀር ማስረሻችን የነበረበት?

“ተው ሀገር አትንሳኝ
ተው ወርሰህ አትንሳኝ”2

1 : ቁርዐን፣ ምዕራፍ 18
2 : ከዘራፊው ማስታወሻ፣ ውብአረገ አድምጥ፣ 9
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 32



ብለን የምንማፀነው ጌታ የለን። አገርን በሁሉም ልብ ውስጥ በመሳል የሳትነው ጉዳይ ነው ያራራቀን። ልክ የአረቡ ሂትለር - ሃጃጅ የሚባለው የሞተ ጊዜ “ሥሙን በክፉ ያነሳ ኀጥዕ እሱ ነው” አሉ የሃይማኖት አባቶች። ባይሉና ባይገዝቱስ? አያት እና ቅድመ አያት የተገደለባቸው ልጆች “ጥንት ጥንት የኛ መሬት ነበር” ብለው የቅሚያ ሥራ ውስጥ ይሻሙ ነበር።

... ከዛስ? ዓለምን ያስደነቀውን Golden Age እናይ ነበር?

ጀማሉዲን የሚሏቸው የሃገራችን የአና አካባቢ ሼህ ወዳጆቻቸው እና ተማሪዎቻቸው በግፍ በትር ሲመቱ ከረሙ። ክፉው ቀን ሲያልፍ

‘ይጻፍ እንጂ’ ሲሏቸው “ቂም አናወርስም” ብለው፣ በሥነልቡናው የላቀ ሀገሩ የራሱ መኾኑን የሚያውቅ ትውልድ ገንብተው ነበር። ሁሉም እንደዚያ ቢኾን ኖሮ በትናንቱ አፍሮ በዜሮ የሚያባዛ የሚኖር አይመስለኝም።

ከመቼው ስቴዲየም ደረስኩ?

ጭንቀት ሲበዛ ሴቶች ያስረሳሉ። የመታገያ አቅም ሲበረታ እነሱ ያስተነፍሳሉ። “ጉልበትህን በሴቶች አትጨርስ ነው አትስጥ” ነው ያለው
ጠቢቡ? ባላገኛት እንኳ ሳስባት ንጋት ይሞላኛል።

ጠዋቶ ኾነ።
ዓይኔ ለያት
ልቤ ዐያት
ሰገድኩላት።3

የሴት ልጅ ልብ ውስጥ ገብቶ ያሰበ እሱ ጻድቅ ነው። እነሱ እንደኛ የሚያሳስበን ያስጨንቃቸዋል? ድካማችንን በጥበባቸው ያቃልሉልናል እንጂ ስለሌላ ጭንቀት ተፈጥሯቸው ይፈቅዳል?

“ምን ዐውቃለሁ ለምን ትጠይቀኛለህ?”

“አንቺ ሴቷ ካልነገርሺኝ እንዴት ልወቅ ታዲያ?”

“ምን ያደርግልሃል? ሲጀመር የምትለውም አልገባኝም።”

3: መንደሪን መንደሪን፣ ምግባር ሲራጅ፣ 56
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 33



ፈገግታዋን ትሰጠኛለች። ሰውነቷ ላይ ያለ እያንዳንዱ ብልት በጥንቃቄ የተገነባ ነው። ፊቷ ላይ ያለ የተቀባ ጥቁር (ከኔ ቀድማ ማርያም የሳመቻት)፣ ምንትነታቸው የማይታወቅ ጥቃቅን
ጭረቶች ድንቅ ሰዓሊ ዕድሜ ልኩን ቢስል አይሰራውም (ወላ
ቦጎሲያንን እና ቫንጎህን ቢውጥ)።

ሜክሲኮ ደረስኩ?

ልብ ሲቆረፍድ በ120 ቁጥር ብርጭቆ ወረቀት ሴቶች
ይጠርጉታል። ከማለስለሻነት ባለፈ ምን ታቅፈዋል? “የወንድ
ሁሉ ህይወት ይሄው ነው? በማግኘት ታክቶ፣ በማጣት ተብከንክኖ መቅረት?...”4 ታዲያ ይሄን ማን ያጠፋዋል? ከነሱ ውጭ....

ዐይኔን ብጨፍነው ፥ ድምፅሽ ይሰማኛል
ጆሮዬን ብደፍነው ፥ ሽታሽ ያውደኛል
ከአጠገብሽ ብርቅ ፥ ናፍቆት ይጠራኛል
የት ነው የሌለሽው?5

ፈገግታዋ ብቻ ብራ ቀን ነው። ማልቀሷ፣ ፍላጎቷ አለመሟላት
ምክንያቱ የመነሻ መዛነቅ መኾኑን ማስረዳቴ፣ ቁጭ ብዬ ማሰቤ
ዕንባ ይጠርግላታል?

ስታለቅስም፣ ስትስቅም፣ ስታወራም፣ ዝም ስትልም፣ ሁሉንም ስትኾን እንደምትወደኝ አውቃለሁ። እኔ ግን እወዳታለሁ? ሳቋን
እንኳ አክላለሁ? እኔ ጋር ልትመጣ ስታበጥር ከማበጠሪያ
ጋር የቀረ ፀጉሯን እኾናለሁ?

ብቻ ፍቅርሽ
ትንግርት ነው
ላፍ ለድርሳን
ሸክ የለውም
እንደሞት እንደመወለድ ልብ ችሎ አይደግመውም።6

4: መለያየት ሞት ነው፣ ዓለማየሁ ገላጋይ፣ 109
5: እንዲህ ያለም የለ፣ ሃብታሙ ሃድራ፣ 109
6: አሚን አሚንዬ፣ ሙሐመድ ኢድሪስ ካሣ፣ 86
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 34

ደብተራው

ተማ፡ሎተ ሀለንተና

ተማ’ሎተ ሁለንተና
ደብተራው

እንደ እናት ዕትብት፣ መና አመላላሽ
እንደ ንስሐ፣ ምህረትን መላሽ
እንደ አባት እንባ፣ ሆድን አባባይ
እንደ ልጅ ዓይን፣ ወዲያው ይቅርባይ
እንደ ነቢይ፣ ነገን አዋቂ
እንደ ‘ዛውንት፣ ዕድሜን መራቂ
ልትጠፋ እንዳለች፣ የምሽት መብራት ወዳጁን ስያይ፣ ይቅር እንዳለ፣ ያይን መራራት እንደ ሠርግ ዳስ፣ እንደ ዋዜማው
አይቶ ለለዬ፣ ሰምቶ ለሰማው
ይሄን ሁሉ ናት!
ይሄን ሁሉ ነው፣እኔም ‘ምጠማው።

2018 ዓ. ም

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 36



ዓለማየሁ ታዬ

ዘፈሐቆ እልፊት ወዘበት እልፊቱ



እንደ ሰሎሞን ደሬሳ የትችት ውርጅብኝ የወረደበት ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ አልገጠመኝም። የጥበብ ሰዎቻችንን ባለ ወርቅ ቀለም አሮጌ ዶሴ ሳገላብጥ “ሰሎሞን፡ ሽሎሞ ሳሊሞን፡ ሱሌይማን” ፈላስፋው! ተመራማሪው! ወለልቱው! አማካሪው! አርታኢው! የደሬሳ ልጅ የትችት ቀንበር ተሸክሞ ወገቡ ጎብጦ ሲንገዳገድ በዓይኔ ኅሊናዬ ይታየኛል። ያልወረደበት ውርጅብኝ አለ እንዴ? እግዚኦ!

“- መልእክት የሌለው የፊደል ትርምስ፤
- ልጅነት ዘጠኝ ወር ሞልቷት መወለድ ነበረባት”
አዲስ ዘመን ጋዜጣ

“እንዲህ ዐይነቱ የግጥም አጻጻፍ ሠነፍ ተማሪን ከማበረታታቱም አልፎ ለተሳሳተ የግጥም አጻጻፍ አዲስ በር መክፈት ነው። . . .”
የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ

“ አቦል ጀባቴም ቅኔ ሆነ?
- ይህ ዘመናዊ ግጥም እንደ አብስትራክቱ ስዕል ግማሽ ገረወይና ቀለም አፍሶ

ዘፈሐቆ እልፊት ወዘበት እልፊቱ

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 38

ውብ ስዕል ነው እንደሚሉት ያለ ነው። - ገጣሚ ወይም ባለቅኔ ቅዘትን ከስሜት ጋር ተዋሕዶ ቃላትን በመደርደር ውስጠ ወይራ ነው ቢል በሥነጽሑፍ ላይ እንደመሸፈት ያህል ያስቆጥራል . . . ”
አሁንም አዲስ ዘመን ጋዜጣ

ምን ይሄ ብቻ አቤ ጉበኛማ “ጎብላንድ አጭበርባሪው ጦጣ” በማለት በሽሎሞ ላይ ሙሉ መጽሐፍ ጽፎበትም የል! ምሁራን ፓሮዲ በሚሉት ዣነር።

ሰውዬው ግን ቆዳው ድርብርብ ነው። ፈረንጆቹ thick skin የሚሉት ዓይነት። ሰሎሞን እንደ አቤ ጉበኛ ከተቺዎቹ ጋር እንካ ሰላንቲያ ሲገባ አይታይም። እሱ ውዝግብ እና እሰጥ አገባ መንደር ድርሽም አይል። ምናልባትም ኅሊናዊ ልዕልናውን በተቺዎቹ ኪሳራ ተቀዳጅቶ በዝምታው ለበቅ ተገቢውን ምላሽ እየሰጠ በሞገስ የኖረ በሞገስም ያለፈ ብቸኛ ኢትዮጵያዊ ጠቢብ ይመስለኛል። በሰሎሞን ላይ የተሰነዘሩ ኂሶች/ትችቶች ፍጹም ኢፍትሐዊ፡ ፍጹም ጭፍን፡ ፍጹም መሰረተ ቢስ ናቸው እያልኩም አይደለም።

የሰሎሞን ደሬሳ ልጅነት በ 1963 ዓ.ም
ስትታተም በወቅቱ የነበሩ አንባቢዎችን
ቀርቶ በጥበቡ ጎዳና የሚጓዙ የሥነጽሑፍ
ሰዎችን ግራ ማጋባቷ ግን እሙን ነው።
እንደኔ እንደኔ እውነትም ልጅነት ያለጊዜዋ የተወለደች ውብ እምቦቀቅላ
ነበረች። ታዲያ ያቺን ውብ ደቂቅ፣
ያቺን አጓጊ ህጻን፣ ያቺን ድምቡሼ ገላ
- በፍቅር ዓይን ለማየት፡ እቅፍ አድርጎ
ለመሳም ሰዎቻችን ቢቸገሩ ታዲያ ምን
ይደንቃል?

የሰሎሞን ደሬሳ በዚያ ዘመን “ልጅነት” ን ይዞ በሐዲስ ልሳን የመከሰት ነገር በግጥሞቹ ይዘትና ቅርጽ ላይ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። ለአብነት ያህል “አርባ ተኩል ግጥሞች” ነበር ያላቸው ስራዎቹን “ለግጥም ተኩል ብሎ ነገር!” የመጽሐፉ መግቢያም እንዲሁ እጅግ ያልተለመደና የተለየ ነበር- ሁላችን እንደምናውቀው። ኢልማ ዴሬሳ ሰሎሞን ካንባቢ ጋር የመፈጣጠሚያ ውሉ ደግሞ ለዚያ ዘመን ፍጹም እንግዳ ነበር። የመፈጣጠሚያ ውል ስንል፦

“በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ለማሰማት፤ ህዝብ በተሰበሰበት ለመዝፈን ወይም ለማንበብ በከፊል ሆነ በሙሉ መልሶ ለማሳተም ወይንም ለመተርጎም የደራሲው ፈቃድ እንዲጠየቅ ህግ ያስገድዳል” የምትለውን ቀጭን ትእዛዝ ማለታችን ነው።
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 39

እንዲያውም የዚህ ጽሑፍ መነሻ “ነገረ አስኳላችን” የደራሲያን የባለቤትነት መብታቸውን ማስከበሪያ ሃቃቸው “መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው” የሚለው መልእክታቸው ነው። (ከታገስን በንባባችን ከዘለቅን ሁሉን እንደረሳለን)

ታዲያ “ሳሊሞን!” በወቅቱ እንግዳ በሆነ መንገድ “በኤሌትሮኒስ
መሳሪያ ለማሰማት. . .” ብሎ የባለቤትነት መብቱን ባወጀበት
አንቀጽ ሳቢያ በግጥሞቹ ላይ ከተሰነዘሩት ኂሶች ባልተናነሰ
ደረጃ መዘባበቻ መሆኑን እንዲያውም ነፍሱን በቁጣ በነዘረ
መጠን መነካቱን የንባብ/የጥናት ደመነፍሴ ሹክ ይለኛል።

ከ “ልጅነት” ኅትመት አንድ ዓመት ቆይታ በኋላ በ 1964 ዓም የታተመው ትንታጉ፣ ጀግናው፣ የፍትሕ መዘምሩ፣ ፈላስፋውና ባለቅኔው ኃይሉ ገ/ዮሐንስ (ገሞራው) “ፍንዳታ” በሚል ርእስ ባሳተመው የግጥም ስብስቡ “እልፊት” በሚል እንቀጽ ስር-

“የግጥሞቹን ደራሲነት አይንፈገኝ እንጂ አንድ መቶ ሺ ቅጂዎችን ካሳተምሁ በኋላ ማንኛውም ፍጡር ቢሆን እንደፈለገው ቢያደርጋቸው አለመቃወሜንና በዚሁም ውሳኔዬ መሠረት አሳልፌ መስጠቴን አረጋግጣለሁ” አላለልህም? ሰሎሞን ኢ ት ስ ር ቅ ኒ /አትዝረፈኝ! ያለውን ገሞራው በ “እልፊቱ!” ይ ኩ ነ ኒ በከመ ልብከ/ እንዳሻህ ይሁንልኝ ብሎን እርፍ!

በ “ፍንዳታ” ብቻ ሳይሆን በ “በረከተ
መርገም” ም ድርሳኑ ላይ ገሞራው
ካንባቢ ጋር ሲፈጣጥም “መብቱ በሕግ
የተጠበቀ ነው” ብሎ በማወጅ ወይም እንደ
ሰሎሞን “ . . . ሕዝብ በተሰበሰበበት
ቦታ ለመዝፈን ወይም ለማንበብ. . .”
በማለት አንባቢን አላደናገጠም። ይልቅዬ

“. . . አሳልፌ ሰጥቻለሁ!” በማለት
ነገር አሳጠረ እንጂ። ዲንቅ! ይላሉ የቀድሞ ሰዎች የዛሬ ኮረዶች “ዋው!” የሚሉትን ነገረ አድናቆት። አሁንም ዲንቅ እጹብ ድንቅ! የገሞራው እልፊት።

ኃይሉ ገ/ዮሐንስ በ “እልፊቱ” ብቻ አይመስለኝም የሽሎሞን ነፍስ በቁጣ የነዘረው። “ፍንዳታ” በሚል ርእስ ባሳተመው መድበሉ መግቢያ ላይ ስለ ግጥም በሰጠው ሰፋ ያለ ሐተታ የሰሎሞን ዴሬሳን “ብቻ ብቸኝነት” ባለ 22 ስንኝ ግጥም ከዮፍታሔ ንጉሤ /ቀኝ ጌታ/
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 40



“ዓይኔን ሰው እራበው ዓይኔን ሰው እራበው

የሰው ያለህ የሰው የሰው ያለህ የሰው. . .” ባለ ኹለት ስንኝ ግጥም ጋር በማነጻጸር ጠንከር ያለ ትችት መሰንዘሩም እንጂ። ብቻ ብቸኝነትን ለረሳን አንባቢዎች በቅንጭቡ እነሆ!

ብቻ ብቸኝነት

. . . .

ይህ ነው ብቻ ብቸኝነት
ብቻነት ሲደወል
ያንድ መሆን ቅዝቃዜ
የጸጥታው ጩኸት
አቆልቁሎ አዘቅት
. . . .

ብቻ ብቸኝነት
ያለፍቅር ጉዞ ያለጎረቤት
ሳያስቡ ወደፊት
በምስጢር ብቻ ብቸኝነት መረሳት የእንቅልፍ ልብ ውዝዋዜ መነጠል የሞት አዙሪት ቅዝቃዜ
የነፍስ ዝግ ብሎ መድማት
የደሙ መጨቅየት
ውስጥ ውስጡን ብቻ ብቸኝነት

. . . .

ልጅነት ገጽ 46

ገሞራው ታዲያ የብቻ ብቸኝነትን ጉዳይ ሲያነሳሳ/ሲኄስ እንዲሁ በደረቁ ሐታታውን አላስነበበም። በወቅቱ በነበሩ ኹለት ዝነኛ የኅትመት በረከቶች ላይ ማለትም በአዲስ ዘመንና በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ጋዜጦች ላይ በዴሬሳ ልጅ ላይ የቀረቡ ሦስት ነቀፌታዎችን ዋቢ በማድረግ ጭምር ሀተታውን/thesis አጠናከረ እንጂ።

የገሞራው ፍንዳታ መጽሐፍ መግቢያ ላይ የተጠቀሱ ጥቅሶችን ለማስታወስ ያህል “ መልእክት የሌለው የፊደል ትርምስ፤

- ልጅነት ዘጠኝ ወር ሞልቷት መወለድ ነበረባት. . . ”

“እንዲህ ዐይነቱ የግጥም አጻጻፍ ሠነፍ ተማሪን ከማበረታታቱም አልፎ ለተሳሳተ የግጥም አጻጻፍ አዲስ በር መክፈት ነው። . . . “
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 41

“ አቦል ጀባቴም ቅኔ ሆነ?

- ገጣሚ ወይም ባለቅኔ ቅዠትን ከስሜት ጋር አዋህዶ ቃላትን በመደርደር ውስጠ ወይራ ነው ቢል በሥነጽሑፍ ላይ እንደመሸፈት ያህል ያስቆጥራል . . . ”

የተነበቡትን ምልከታዎች ዋቢ በማድረግና “ከላይ የተሰነዘሩት አስተያየቶች በእውነት ባዶ አይመስሉኝም። ይህንን ለማለት ያበቃቸው በቂ ምክንያት እንዳላቸው መገምገም አያስቸግርም” በማለት ገሞራው ሳሊሞንን እንደምን አድርጎ ተቸው? /በከፊል ለመቆንጽል ያህል-

“. . .ቃላት ያለቦታቸው ታጉረዋል። ‘ ሲንሳፈፉ መታመቅ. . . መበላት በጥልቀት- -ያራስነት ፍርሃት - - በነፍስ ደም ቅራሪነት - - -’ የተንጠራወዘ ፍልስፍና ይመስላል - ምናልባት የማይገቡ ቃላትን በመደርደር ማዋሃድ ፍልስምና የሚመስላቸው ሰዎች ቢኖሩ። ይኸኛውም ባለግጥም የዚያ ብጤ ነው። የብቸኝነት ስሜት ሃሳብ ኩነት ኢምንትነት - - - በዚህ አይነት አገላለጽ አግዝፎ ለማሳየት ከመሞከር ይልቅ. . . ግልጥነትን በግብር ማሳየት ይበልጥ ይቀላል።

“ሲንሳፈፉ መታመቅ
ዳግም ያራስነት ፍርሃት
መታነቅ መወበቅ
የፊቱን እንደረሱት
ብቻ ብቸኝነት” ሰሎሞን ዴሬሳ/ልጅነት

ይለጥቃል ገሞራው -

“ከነበረው የግጥም ሥርዓት ማፈንገጥም ብቻውን ገጣሚ አያስመስልም። የሐሳቡን ጥልቀት ብንመረምር የሐሳብ ቅጥልጥልነት ተከታታይነት ግልጽነት የሚጎድለው በመሆኑ ግልብ ነው። ቅኔ አለበት እንዳይባል የፈረንጅኛ ተጽእኖ ስለእሚያሳይ ቅኔነት ያፅፅበታል። ገሞራው/ፍንዳታ

“መዋጥ መበላት በጥልቀት
እገዛ ራስ ነፍስ ማጥ
እልም ብሎ መስመጥ
ይህ ነው ብቻ ብቸኝነት
ብቻነት ሲደወል
ያንድ መሆን ቅዝቃዜ” ሰሎሞን ዴሬሳ/ልጅነት

“በርግጥም ‘ታሪክ እራሱን ይከልሳል’ እንደሚባለው ሁሉ ያማርኛ የግጥም ታሪክ ከደረሰበት ደረጃ ወደኋላ ተመልሶ የቤት መምታቱን የስንኝነቱን ረድፍ
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 42



አለማዛባቱን የምጣኔውን የዜማውን የቃላትና የሐረግ አመራረጡን ከልሶ ወደጥንቱ ‘የማነው በሬ እግዜር የማረው ፤ እቅብቅብ ገብቶ ይነፈንፋል’ ለመገኘት የበቃ ይመስላል።” ገሞራው/ፍንዳታ

ገሞራው ያወረደው የትችት ውርጅብኝ “እልፊት” ከምትለው የጥበብ ስራ ባለቤትነቱን አሳልፎ የመስጠት ነገር (በሰሎሞን ዴሬሳ ዐይን) አሳልፎ የመስጠት ዘበት! ጋር ተደርቦ ሰሎሞንን በእጅጉ ያስቆዘመው ይመስለኛል። ፍንዳታ ከታተመ ከ ሦስት አሠርት ዓመታት በላይ በኋላ የታተመው የሰሎሞን ኹለተኛ መድበል “ዘበት እልፊቱ” በሚል እንግዳ የሆነ ርእስ እንዲከሰት የገሞራው እልፊት ምክንያት መሆኑ የጥናት/የምርምር ደመነፍሴ ደጋግሞ ሹክ ይለኛል።

የዚህ ጽሑፍ መነሻዬ/የተብሰልስሎት እርሾዬ ግን “መብቱ
በሕግ የተጠበቀ ነው የሚለው አዋጅ ነውና ይህንን ጽሑፍ
ሳበሳስል የሰበሰብኳቸውን አዋጆች እኔም በተራዬ ላውጅላችሁ!

በነገራችን ላይ የኃይሉ ገ/ዮሐንስን ግጥሞች በማከብርበትና
በማደንቅበት ልኬት የሰሎሞን ዴሬሳንም አከብራለሁ
አደንቃለሁ። በኹለቱም የጥበብ ሰዎቻችን ብቃት ችሎታና
ባለቅኔነት ላይ ምንም ጥርጣሬ የለኝም። እንዲያውም ገሞራው
ብሽቅ አድርጎ የተቻትን “ልጅነት” እኔ ዲንቅ አድርጌ
ልፈክራት እችላለሁ። ሰሎሞን ከዋኘበት ጅረት የጠለቀ ሁሉ
ሰውዬውን ሊረዳው እኮ አይገደውም።

ንግባእከ ኅበ ነገረ አስኳል!

የቀድሞ ደራሲዎች፣ መተርጉማን፣ ገጣሚዎች በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ከአንባቢ ጋር ሲጎዳኙ የአደራ ቃላቸው የመፈጣጠሚያ ሃቃቸው “መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው” የሚለው ሐረግ ነበር።

“በጽሑፍ ፈቃድ ወይም በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ዐዋጅ ቁጥር 165/1960 ርእስ 11 የሥነ ጽሑፍና የኪነጥበብ ሥራዎችን ባለቤትነት በተመለከተ ከአንቀጽ 1647 እስከ አንቀጽ 1674 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ከመጽሐፉ አንድ አንቀጽ እንኳን መልሶ ማሳተም መቅዳት ወይም በሌላ መልክ ማሳተምና ማሰራጨት አይፈቀድም።” የሚለውን ዐረፍተ ነገር/ማስጠንቀቂያ ያስጀመረው ሻማ ቡክስ ይሆን?

©በልእስቲ አሸብር 2018 ደግሞ ከረፈደ የተጀመረ መላ ነው። ያሸብር ልጅ በልእስቲ ተሳስቷል ትክክለኛው አገላለጽ “© 2018 በልእስቲ አሸብር” መሆን ነበረበት። በቅርቡ እየተለመደ የመጣ የዚሁ ኢትዮጵያዊኛ ሞክሼ ደግሞ “(መ)
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 43

2018 ማንጠግቦሽ ታደለ” ነው/በትክክለኛው አጻጻፍ!

በጀለሶቻችን አገር መጻሕፍት ሲታተሙ አታሚዎች የማያልቅ ነገር (ክርክር) እሰጥ አገባና የካሳ ክፍያ ጣጣ ውስጥ ላለመግባት ደራሲያንን ከ Library of congress የይለፍ ወረቀት/clearance እንዲያመጡ ያስገድዳሉ። በነሱ አገር በእንግሊዝኛ ቋንቋ ያሳተምኳት ሚጢጢ መጽሐፍ ብጤ እንዲህ ዐይነቱ የይለፍ ሊቼንሳ አላት። ታዲያ በዐይነትም በ “genre” ም ተመሳሳይነት ያለው ሌላ ድርሳን አድርሼ ወደ library of congress ስልክ ብመታ

“Authorship and ownership is automatic; you don’t have to get it registered at Library of Congress every time you write a book, unless publishers require it” አለችኝ። ከወዲያኛው ጥግ መልስ የሰጠችኝ ባለሙያ።

እውነትም የደራሲው የባለቤትነት መብት እኮ አጠያያቂነት የለውም። ጎበዝ! ምን ልፍት ሲያደርገን ነው ያልተነክብንን መብታችንን ስናውጅ የኖርነው? የሚል ሐሳብ ዛሬ ድረስ ይገተግተኛል።

“ዘፈሐቆ ወዘሰረቆ ውጉዘ ለይኩን በሥልጣነ ጥበብ ወኪን” የምትጣፍጠኝ ምናልባትም ይስማእከ ወርቁ ያስጀመራት አዋጅ ትመስለኛለች። የሷ ተመሳሳይ ሐሽማል ላይ ያነበብኩት (መርገምት) ነው።

“ይህ መጽሐፍ ጥበባዊ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው። የሰረቀም፣ ያሰረቀም ተከታትለው እንጦሮጦስ ይወርዳሉ” ማዕበል ፈጠነ/ሐሽማል።

ሌላው የአዋጅ ጋጋታ ያስተዋልኩበት አንቀጽ ተከታዩ ድርሳን ላይ ያነበብኩት ይመስለኛል።

1.“©አስማረ ሞሴ ዘሩ ፳፻፲፬ ዓ.ም”/ 2. “ኩሉ መብቱ በሕግ እቁብ ውእቱ”/
3. “መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው”/ 4. “All rights reserved” በማለት በልሳነ ግእዝ ፡ አምሐራ ወ እንግልጣር አዋጁን አራት ጊዜ ደርድሮልሃል። ስብሐት! ለጥበብ አምላክ።

ከሩሲያ የተተረጎሙ አብዛኞቹ ሥራዎች “© የፕሮግሬስ የመጻሕፍት ማዘጋጃና ማሳተሚያ ቤት፤ የአማርኛ ትርጉም እ ኤ አ 19 ?? ዓም” ይሉ ነበር።

የመንግሥቱ ገዳሙ “ሌላው እንደሚያይህ፤ ጠባይና የሕይወት አቋቋም” መጽሐፍ “ያለደራሲው ፈቃድ በእንግሊዝኛ መተርጎም ወይም መጽሐፉን ማባዛት አይፈቀድም” ትላለች።
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 44

በፈረንጅ አገር የታተመች “የንጉሥ ልጅ” መድበል ደግሞ

“All rights reserved under the International and Pan-American copy right conventions.” የሚል መብት አስረጋጭ አንቀጽ አስነብባለች። የገሞራው ‘እልፊት!” የዚህ ኹሉ ሐተታ መንስኤ ነው። ዞሮ ዞሮ “ዘፈሐቆ ወዘሰረቆ ውጉዘ ለይኩን በስልጣነ ጥበብ ወኪን” የሚለው ሐረግ “መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው” ከሚለው አዋጅ ምንም ልዩነት የለውም።

“ያለባለቤቱ ፈቃድ መልሶ ማሳተም ክልክል ነው” የሚለውንም ማስጠንቀቂያ “እንደገና ለማሳተም መብቱ የአዘጋጂው ነው” ከሚለው ትእዛዝ ጋር በትይዩ ነው የምንረዳው “All rights reserved” ደግሞ ኹሉን ባንድ ይጠቀልላል።

ይቆየን!

7alemayehu@gmail.com

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 45



ሳምራዊት ንጉሤ

አስመለጠኝ!

አስመለጠኝ!
ሰካራም አልወድም ያስጠላኛል። በዛ ምክንያት ልጅነቴንም አልወደውም። በእሱ ምክንያት በታላቅ ወንድሜ ምክንያት...።ሳየው ደሜ ይፈላል። አሁን ተለውጫለሁ ቢልም ያ ልጅነቴን ያበላሸብኝን ወጣትነቱን እያሰብኩ እናደዳለሁ።

ሲመሽና ሲጨልም እናቴ፣ እኔ እና ታናሽ ወንድሜ መጨነቅ እንጀምራለን።”ደሞ ሰክሮ መጥቶ ከአባቱ ጋር ይጣላ ይሆን?” እያለች እናቴ ስትጨነቅ ታመሻለች። “ ተነስተሽ አተኝም?” የሚለው የአባቴን ንግግር ሰምታ ለመኝታ ስትነሳ እኛንም “ተነሱ ተኙ ደግሞ መቶ እንዳይበጠብጠን” ትለናለች። በጣም ካልባሰበት በስተቀር ከተኛን በኋላ በር አያንኳኳም። ከኋላ ካለው ሰርቪስ ክፍሉ ገብቶ ይተኛል።

ብዙ ጊዜ ግን ማስታውሰው እናቴን በልመና አስጨንቀናት እኛት ትታን ከተኛች በኋላ፣ የቤቱን መብራቶች በሙሉ አጥፍተን እኔና ወንድሜ ቁጭ እንላለን። የቲቪውን ሪሞት ፖወር በተኑን በአውራ ጣቴ ለመጫን እጠባበቃለሁ። ገና የውጪው በር መከፈት ሲጀምር ድርግም አደርገዋለሁ።

የባሰበት ቀን ያንኳኳል። እናቴ ጋቢዋን ደርባ ለመክፈት ትነሳለች። “አባትህ ተኝቷል ድምፅህን ቀንስ” ብትለውም አይሰማት። “ እንደውም ይስማ ለባልሽ ማገዝሽ ነው?” እያላት ወደ ውስጥ ይገባል። እኛ ወደተኛንበት ክፍል ይመጣል።ተነሱ ይላል ቀን ያጠፋነው ካለ በዛ ስካሩ ሊመክረን ይታገላል።እራት አምጡ ብሎ ቀርቦለት “አባሉኝ” እያለ በእኩለ ለሊት ነፍሳችንን ያስጨንቃታል።

የወንድሜን ወጣትነት አልወደውም። ምንም እንኳን ልክ ቢሰራ ለእኔ አሁንም
ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 47

እናቴን የሚያስጨንቃት፣የውሻ ጩኸት በሰማች ቁጥር በመስኮት ምታጮልቀዋ እናቴ ዓይኔ ላይ ትመጣብኛለች። በሰከረ ቁጥር ቀን ደክሞት በሰላም ከአልጋው ተኝቶ ያለውን አባቴን አስነስቶ ሲነዘንዘው አባቴም በፀባይ “ግባ እና ተኛ ጥዋት እናወራለን”*ሲለው የአባቴ ትህትናው ይመጣብኛል።

“እኔ ወንድምሽ አለሁልሽ” ሲለኝ አፌን ሞልቼ “የለህልኝም” እለዋለሁ። ያለ ሀሳብ መተኛት እንዳልችል አድርጎኛል። ያኔ በእሱ ምክንያት ይኸው ዛሬም በእራሴ የህይወት እሩጫ አልተኛም።

ሰካራም ሳይ ውስጤ ገፍትረሽ ጣይው ጣይው ይለኛል። ከሰካራሙ ሰውዬ ጋር በሀሳብ ቤቱ ድረስ እሄዳለሁ። የቤተሰቦቹ ጭንቀት ይመጣብኛል። ሲያንገበግባቸው ይታየኛል።

ሰው ጠጥቶ ሞቅ ሲለው ይጫወታል ሲሉ” አዎ ይጫወታል ቤተሰብ ላይ፣ ልጅነት ላይ ፣ህይወት ላይ ፣ጊዜ ላይ ይጫወታል” እላለሁ።

ወንድሜ እንደዚያ ነው። ቀን የተዘጋው አንደበቱ ማታ ይከፈታል። “እኔ እኮ፣ አንቺ እኮ ለእኔ...” እያለ ይንበዛበዛል። ሁሉም ስለሱ፣ ስላደረገው እና ስላልተደረገለት ነገር እያነሳ ይለፈልፋል።

ሰኞ ትምህርት ቤት ከጓደኞቼ ጋር ስገናኝ ቅዳሜ ማታ ስላዩት ታላቅ ፊልም ሲያወሩ “እኔ እንቅልፌ መጥቶ በጊዜ ነው የተኛሁት አላየሁም” እላለሁ።እንዴት ብዬ ወንድሜ ሰክሮ እንዳይበጠብጠን እናቴ አስተኛችን ልበል። ግን የለሊቱን አጋማሽ በእልህ፣ በንዴት፣ በእድለ ቢስነት ስሜት ጨለማ ውስጥ አፍጥቼ እንዳመሸው ለማን ልናገር?

ልጅነቴን ለመካስ አሁን ሁሉን በፍላጎቴ ለማድረግ ሳስብ ነገም እንደማገኘው ስለማውቅ አያጓጓኝም። ጉጉቴ ያኔ ቀረ ከአመለጠ አመለጠ ላይ።

ወንድሜ አስመለጠኝ። እንቅልፌን፣ያለሀሳብ መተኛትን ፣ያለሰቀቀን መኖርን አስመለጠኝ…

ልጅነቴ አመለጠኝ!

የወር ሰው ይበለን

ባይራ ዲጂታል መጽሄት

ቅጽ ፪ ቁጥር ፱ 48

ያላባቸው እጆች...

ቴዎድሮስ የማነብርሃን

...ጥሪዋ ውስጥ አንዳች የመገፋት መንፈስ ያደፈጠ መሰለኝ።...ሳቅ የሌላቸው፣ደስታ የራቃቸው፣ሲቃ ያናወዛቸው ብዙ የመከራ ድንኳኖች አርባቸውን ሊደግሱ ሽር ጉድ የሚሉ መሰለኝ።በጀርባዋ አዳፋ በጎረሰ እራፊ ጨርቅ ለዚህ ዓለም እንግዳ የሆነ ልጇን አዝላ የበሯ መውጫ ጠርዝ ላይ ደፉን ረግጣ፣ ጉበኑን በቀኝ እጇ እንደያዘች ቆማ ዳግም ስትጣራኝ ነበር ያስተዋልኳት።

የልጇን አባት የዛሬ ዓመት ነበር በሞት ያጣችው።ነፍሱን ይማረውና አንድ ዓይና ቸኮል (በኢትዮ ኤርትራ የወንድማማቾች ጦርነት ላይ
የዘመተ ሲሆን፣ የግራ በኩል ዓይኑ ላይ የፈንጅ
ፍንጣሪ አግኝቶት ብርሃኑን በማጣቱ ነበር የሰፈሩ
መቲ ልጆች “አንድ አይና” ብለው ስም ያወጡለት)
ደግነትና ርህራሄ ምግባሩ የነበረ ከሰፈራችን ብቸኛ
ከጦርነቱ ተርፎ የተመለሰ ሰው ነው።እድሜው
በሰላሳዎቹ መጨረሻ ያለ ቢሆንም፣ በወቅቱ ከእሱ በዕድሜ የስድስትና የሰባት ዓመት ታላቅ የነበረችውን አበራሽን አግብቶ መኖሩ በሰፈሩ ሐሜተኞች ዘንድ ግርታን ፈጥሮ ነበር።በነሱ እፍ ባለ ፍቅር የሐሜተኞች ጥርስ ዕድሜው አጠረ እንጂ እቅዳቸው አንድ ምዕተ ዓመት ማማት ነበር።

ከመሞቱ በፊት ግድግዳው ላይ ከተሰቀለው፣ በካራቴ አነሳስ እግሩን ሽቅብ ሰቅሎ ከተነሳው ፎቶና ከመከላከያ መልስ ይዞት ከመጣው የመከላከያዎች ዩኒፎርም ልብስ በቀር፣ ምንም ጥሎላት የሄደው ሀብት አልነበረም።ጀርባዋ ላይ ያዘለችው ልጇን ለማሳደግ እየከፈለች ያለው መስዋዕት የእናትነት ግርማዋንና እውነትነቷን ፊቷ ላይ ኑሮ ያሳረፈው ሰንበር ያሳብቅባታል።መከራዎች መምጫቸውም ሆነ መሄጃቸው አይታወቅም፤እናትነት ሞገስ ነው፤ተከብሮ ማስከበር፤ዝቅ ብሎ ከፍ የማድረግ ጥበብ ነው እናትነት።ከጀርባዋ የተለጠፈው ህፃን ምክንያቱ ባልታወቀ ምክንያት ያላዝናል።ግራ ቢገባት ነበር የጠራችኝ።

“አቡቹ...”

አለችኝ ልጇ ዝም እንዲልላት ወደፊት ወደኋላ እየናጠችው።

“...ልጄ እንደው ሰው መሄጃውንም ዕጣውንም አያውቅ...።”

ያላባቸው እጆች...

ባይራ ዲጂታል መጽሄት 50 ቅጽ ፪ ቁጥር ፱

አለችኝ ገና የመጣው እግሬ ተረጋግቶ መሬት ቆንጥጦ ሳይቆም።የዛሬው ምሬት የተቀላቀለበት ንግግር ነው።ከዚህ በፊት አንድም ቀን በኑሮዋ ላይ አምርራ ተናግራም ሆነ ከፍቷት አይቻት አላውቅም።ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ የልጇ ጩኸት ምርር ማለቱ፣ ሌላ ነገር እንደሆነ የገመትኩት ከንግግሯ ጀርባ የደበቀችው ስሜቷ ገንፍሎ በወጣው እምባዋ ነበር።

“አቡቹ ምግብ በአፌ ከዞረ ይሄው ሶስተኛ ሌሊት እየመጣ ነው።ልጄም ሳይራብብኝ አልቀረም።ጡቴን ስቦ ስቦ ይሄው ምንም ሳያገኝ ሲቀር ነው እሪሪሪ የሚለው።ጡቴም እንደምታዬው ተጨምቆ ተጨምቆ ለትቷል።ድሮስ ከየት ያምጣው? ሲያገኝ አይደል የሚሰጠው? ካልሰጠኸው ማን ይሰጥሃል? የገዛ አካልህ እንኳ ካላጎረስከው ንፉግ ነው።እግዜሩስ ብትል ካልተከተልከው ልጄ ብሎ መች ያቅፍሃል? አያቅፍህም!የሱ ካልሆንክ ያንተ አይሆንህም።ባጭሩ ባደረከው ልክ ነው የሚደረግልህ።”አለች ደረቷ ላይ ተሰቅሎ የዋለ የልኳንዳ ቤት ስጋ ይመስል ደርቆ የተለጠፈ ጡቷን በእጇ ጭምድድ አድርጋ ይዛ።

መሄጃ ያጡ የመሰሉ እግሮቿ የበሩን ደፍ ቆንጥጠው ቆመዋል።የሚጨብጡትን ያጡ እጆች ጉበን ተደግፈዋል።የሚናገሩ አንደበቶች ዛሬ ላይ ቃላት ጠፍቶባቸው በእምባ ርሰዋል።ብዙ የተራቡ ምንዱባኖችን ያጎረሰ እጅ ዛሬ አጉራሽ ፍለጋ ይወራጫል። ግን ሰው ከፋ። እጅ ባጎረሰው ተገፋ።ግራ ገባኝ። ከዓመታት በፊት እዚህ የእትዬ አበራሽ ቤት ደስታ እንደ ጉድ የሚዛቅበት ቤት ነበር።ማንም የጠማው መንገደኛ ውሃ ሳይሆን ወተት እየቀረበለት እንደፈለገ ይራጭበት ነበር።ርቦት የደረሰ እንግዳ ከጮማው፣ ከቅቤው፣ ከወተቱ ነበር የሚቋደሰው።ዛሬ ጊዜ ራሱን ገልብጦ የእነ እትዬ አበራሽን ቤት መና አስቀረ።ጊዜ እባብ ሆነ።ጊዜ ዘንዶ ሆነባቸው።ፍዬል ወልዳ ወልዳ...።አቤት ጊዜ።

“ግራ ቢገባኝ ነው የጠራሁህ።አቡቹ የሆነ መላ ፈልግልኝ፣መቼም አንተ ለችግሮች መውጫ ቀዳዳ አታጣም።ፈጣሪ ሲፈጥርህ ለችግሮች መፍቻ ቁልፉን ሰጥቶህ ነው የፈጠረህ።” አለች ድጋሜ አይን አይኔን በፈዘዙ አይኖቿ እያየች።

ብዙ የተራቡ ሰዎች ይኖራሉ።የተቸገሩ በየስርቻው ጠያቂ አጥተው እንደወደቁም አውቃለሁ።የእትዬ ግን ልክ አልነበረውም።ለዚያውም የዚህች ቅርፊታም ዓለም ምንነትን ያላወቀ አንድ ፍሬ ልጅ ጀርባዋ ላይ ለጥፋ ቅዝዝ ማለቷን ሳስተውል ግራ አጋባኝ።ወዲያው የመጣልኝ ለእናቴ መንገር ነበር።ወደ ቤት ተመልሼ ለእናቴ ነግሬያት መሶብ ውስጥ ከተከመረው እንጀራ አጣጥፌ ማምጣትና የቀድሞውን ደስታ መመለስ ነበር።ቆይቼ ግን ስረዳው ለካስ እፍ ሲያደረጋቸው የነበረው የእናቴና የእትዬ አበራሽ የጉርብትና ፍቅራቸው ውስጥ አሜኬላ በቅሎበታል።ባሏ ከሞተባት በኋላ እናቴ ፊት ነስታታለች።ምክንያቱን ግን ሊነግሩኝ አልፈለጉም።

ባይራ ዲጂታል መጽሄት 51 ቅጽ ፪ ቁጥር ፱

ቤታችን ያለው ቡና ቤታቸው ነበር።እኛ ቤት የነበረው ጋሎን ሙሉ የተነጠረ ቅቤ እነሱ ቤትም እንደነበር አስታውሳለሁ።በሁለቱም ጓዳ እህል ስላላቸው ፍቅር ነበራቸው።ፍቅራቸውን ያላጎደለው የሞላው ጓዳቸው ነበር።እናቴ ወረተኛ እንደነበረች የተማርኩት ያኔ ነበር።ሰው ሆኖ እስከነ ግርማው የሚፀና የለም።ሰው ሆኖ በተቃርኖ መንገድ አልጓዝም ማለት አይችልም።ሰው ራሱ ከተቃርኖ ጋር ነው የተፈጠረው።ተቃርኖ የሌለበት ቤት የለም።ተቃርኖ ያልገባበት የህይወት እንጀራ የለም።በተድላ ታጥሮ በተድላ የሞተ የሰው ልጅ የለም።ህይወት ሙሉ ሸክላ አይደለችም፤ ስባሪም አለባት።ስባሪ የሌለባት ህይወት ሽራፊ ናት።ህይወት ጥፍጥናዋ ጉድፍ ሲኖርባት ነው።ፈተና ሲያገኛት ነው።እንከን አልባ ኑሮ የትም የለም፤ የትም አይኖርም።በቃ የሆነው እንደዚህ ነበር።ጠዋት በጣም ጠዋት፣ የጠዋቷ ጮራ በቤታችን መስኮት የጨረር እግሮቿን ሳትሰድ አስቀድሜ ለእትዬና ለጨቅላው ልጅ የሚያስፈልጋቸውን (እናቴ በሙሉ ልቧ ባትቀበለውም) ከእናቴ ጋር ተነጋግሬ እያዘጋጀን መውሰድ ጀመርኩ።

ሰው መሆኔን አምናለሁ።ሰው ለሰውም መኖር እንዳለበት ነፍሴ ታምናለች።ነፍሴ የምታለቅስበትንና የምትደሰትበትን፣የሚያሞቃትንም ሆነ የሚያበርዳትን ምክንያት አውቃለሁ።ደግነት ለራስ ነው እያለች ነው እናቴ ያሳደገችኝ (ውሸት እንደነበር እስክደርስበት ድረስ)።አዎ ክፋትም ሆነ ደግነት የወደፊት ገመዳችን ነው።ወደፊት በእጃችን ርዝመትና እጥረት ነው የሚሰፈርልን።እና ያንን የክፋት ከዘራ አልፈልገውም።ወደዚህች ምድር የመጣሁት አንዴ ነው ስሄድም አንዴ ነው።ሁለቴ መጥቶ ሁለቴ የሄደ ፃድቅ የለም።ለዚያ ነው ከክፋት ደግነትን የማስቀድመው።ምንም ቢሆን ግን እንደ እናቴ አስመሳይ መሆንን አልሻም።

“እትዬ ከእናቴ ጋር ያለሽ ፀብ አይመለከተኝም፤ እሱ ሌላ ምዕራፍ ነው።ጋሼ በነበረበት ጊዜ ያላችሁን ወዳጅነት አውቀዋለሁ።ጊዜ አልነበረም ሊገታችሁ የነበረበት።እናንተ ብቻችሁን ለሰው ምሳሌ ልትሆኑ የምትችሉ ሰዎች ነበራችሁ።አሁን ያ አይደለም ፍላጎቴ። አንቺንና ይህንን ህፃን በተቻለኝ አቅም ከገጠማችሁ ችግር ማትረፍ ነው።ቢሆንም ግን እንዴትና በምን መንገድ የሚለው ጥያቄ ያሳስበኛል” አልኩ።ፀጥ ብላ ስታደምጠኝ ዝምታዋ አስፈራኝ።በሰው የመገፋት ስሜት ነው ፊቷ ላይ የማስተውለው።በተለይ የመገፋፋት ገፃቸው ላይ እናቴን ተጠያቂ የሚያደርግ ነው የማየው።

“ልብ የገዛ ልብ አጣ ልጄ።እናትህ ጀርባዋን የሰጠችኝ ጥፋት ሰርቼ እንዳይመስልህ። በድህነቴ የተነሳ ነው።አግኝተህ አትጣ፤አግኝተህ ስታጣ ጎታቹ ብዙ ነው። ከንፈር መምጠጥ፤ የቤትህን ሽንቁር የሚደፍን ይመስል፣ ያየህ ሁሉ ከንፈሩን ሲመጥ ታያለህ።ከንፈር መምጠጥ የሀዘን ብቻ እንዳይመስልህ። ብዙ ትርጉም አለው።መውደቅህን በመምጠጥ ያስረዳሃል።አግኝተህ ማጣትህን በዚያ መንገድ ይነግርሃል።አግኝተህ በማጣትህ ሊያግዝህ እንደሆነ እንድታስብ ያደርግሃል።ብቻ

ባይራ ዲጂታል መጽሄት 52 ቅጽ ፪ ቁጥር ፱

ተወው ልጄ፣ ሰው ዛሬ ያበራለት የሀብት ፀሐይ ነገ የምትጠልቅበት አይመስለውም መሰለኝ ብዙ ያወራል።ሊተችህ ይሽቀዳደማል። ባላጠፋኸው ጥፋት የጥፋተኝነት ስሜት ተሰምቶህ ራስህን በደለኛ እንድታደርግ ሸንጎ አቁሞህ እንድትሞግት ያደርግሃል።”

ሲያለቅስ የነበረው ልጇ ፀጥ አለ።በህፃኑ ፀጥታ የኔ ሀሳብ ቀጣይ ለምፈልገው መላ አዕምሮዬ ላይ ስራ ሲያበዛብኝ የእናቱ ልብ ደግሞ በመተኛቱ የእፎይታ መረጋጋት ውስጥ የገባ መሰለኝ።

“ግራ ቢያጋባም ሌላ ምርጫ የለኝም።” አልኩ ያመጣሁትን ሀሳብ ላካፍል እየቸኮልኩ። ምን እንደሆነ ለመስማት በሚያቆበቁብ እይታ ታጅባ ፀጥ ብላ እያስተዋለችኝ ሳለ...

“ለልጅሽ ሲሉ ያደርጉታል ብዬ አምናለሁ።አቡላን ታውቂው የለ የሻምበል ባሻን ልጅ? እሱ በክፍያ ልብስ እንደሚያሳጥብ አውቃለሁ።የሆነውን እነግረውና ሌላ ሥራ እስክናገኝልሽ ድረስ እዚያ እየሰራሽ ለልጅሽ የሚያስፈልገውን ታደርጊለታለሽ” አልኩ። ምንም እንኳ ሀሳቤ ያንን ያክል በብልሃት የታሸ ባይሆንም፣ አንገት ማስገቢያ ይሆናል ብዬ በማሰብ።የሀሳብ አንገት ከገባ የቀረው በራሱ እየተሳበ መግባቱ አይቀርም።የችግር ጠልፎ መጣያ ገመድ ሥራ ነው የሚል ብሂል አለኝ።ማንም ከሰራ ከፊቱ የተከመረ የድህነት ጋራውን ደርምሶ መጣሉ አይቀርም።ጥቂት ሰርቶ ብዙ መርካትን አልሻም።ለተቸገሩ ሰዎች አንድ ኪሎ ዱቄት ከአንድ መለኪያ ዘይት ጋር ወርውረው በየሚዲያው ሱፋቸውን ዠቅ አድርገው ማይክ በመጨብጥ፣ “ለአምስት ሺህ ለተቸገሩ አባወራዎች የትንሣኤ በዓልን ምክንያት በማድረግ እርዳታ አደረግን” እንደሚሉ የዘመኑ የአስተሳሰብ አራዳዎች ማለት አያስደስተኝም።

ድህነት ላይ መቀለድ አንድ ነገር ነው።ደሃና ምስኪን ህዝብ ላይ ማላገጥ ከአእምሮ ማነስ የሚመጣ የአስተሳሰብ ልምሻ ነው።ሰው እንዴት በገዛ ማንነቱ ላይ ይቀልዳል? ወንበር ስቦ አክብሮ ያስቀመጠህን ህዝብ እንዴት ታሾፍበታለህ? ሌላው ቢቀር ድህነቱን አምኖ የሚኖርን ህዝብ “እየረዳሁህ ነው” ብለህ እንዴት ቁስሉን ትነካካበታለህ?መቼስ ነው ለእውነት የምታድረው? እላለሁ በውስጤ።

ቀጠል አድርጌ...በቀጣፊዎች ስብስብ ምክንያት የምትታመስና የምትዋ’ሽ ሀገር ተሻጋሪ እንጂ አሻጋሪ የላትም።ሌቦች በቀደዱት አጥር የሚያልፉት ትውልዶች ሌቦች መሆናቸው፣ዘረኞች በዘር ትብታብ ጠፍረው “በገነቧት” የአስተሳሰብ ቅማል የወረራት ሀገር ውስጥ የነገሱ ትውልዶች የአባት መንገድ እንጂ የራስ መንገድ የላቸውም።ሰው መንገዱ የሚያምረው መሪው ያማረ ሲሆንለት ነው።ሰማዩ ቁልቁል የሚሸናው የረጠበ የደመና ክምር ሲኖረው ነው። አስተሳሰብ ሲከረፋ

ባይራ ዲጂታል መጽሄት 53 ቅጽ ፪ ቁጥር ፱

ትውልድ ይቀጭጫል፤ክፋት ሲያረፋፍድ ሀገር ትተርፋለች። እላለሁ ሌላው ትውልድ ቢሞት እንኳ ይህንን በእትዬ ጀርባ ያለውን ጨቅላ የማትረፍና የመታደግ ሀላፊነት እንደተጣለብኝ ራሴን እያሳመንኩ።

እናም
ከእለታት አንድ ቀን፣ ነገር እንዲህ ሆነ
ለሰው ልጆች ተስፋ፣ ተስፋ በቀን ውስጥ ተነነ
ሰው ህይወት ሊቀይር፣ ነፍስ እየገበረ
በራስ እጣ መንገድ፣ መንገድን ተማረ።

ከስድስት ወር በኋላ የእትዬ አበራሽ ተስፋ ጠቆረ። መሄድ የሚችሉ እግሮች ቆመው ቀሩ። ነገን የሚያይ ራዕይን የሰነቀ ልብ ደርቆ ቀረ።ማን በማን ሰበብ ይፍጠር? ማን የማንን ሀጢያት ይሸከም? አንደበት የዘጋ፣ ከንፈር ያቆረፈደ፣ የሰውን ልጅ ከእግዜር ፍጥረት ጋር ያቃቃረ ትልቅ ተዓምር ተፈጠረ።

ፀሐይዋ ልትጠልቅ ከምዕራቡ አቅጣጫ አቅላልታለች። የጀምበሩ ወርቃማ ቀለም በደመናው ሽንቁር ሾልኮ እየወጣ አካባቢው ላይ በፈጠረው ነፀብራቅ ልዩ ድባብን ቢፈጥርም፣ ቀኑ ክብድ በሚል በአንዳች ጥላሞት ተከቧል።በምዕራቡ ላቅላላው ፀሐይ ማነቆ ሊሆን ጥቁሩ ደመና በምስራቁ አቅጣጫ ፀሐይዋን ሰልቅጦ ሊውጣት እያደባ ይመስላል።አካባቢውን መስክ ላይ የተሰማሩ ነጫጭ በጎች ሞልተውታል። መስኩ በጥበበኛ ሰዓሊ የተሳለ ይመስል፣
ድምቅ ያለ አረንጓዴ ቀለም የተረጨበት ያስመሰለው
ሳር ለጥ ብሎ ይታያል።መስኩን በጎች ይሙሉት እንጂ አይግጡም፣አይጮሁም፣ፀጥ እንዳሉ ነው።

ህፃን ልጅ ያዘለች አንዲት ስስ ነፍስ ያላት እናት
አረንጓዴውን መስክ አቋርጦ ቁልቁል ወደሚፈሰው ወራጅ ወንዝ ውሃ ልትቀዳ አመራች።ከወትሮው የውሃው ፍሰት ይለያል።አንዳች መልዕክት ያዘለ ይመስል ፍጥነቱ የእሽቅድምድም ይመስላል።ወራጅ ውሃው ግሳት ጨምሮበት ቁልቁል በታላቅ ድምፅ ታጅቦ
ይንፎለፎላል።ውሃ የምትቀዳ እናት፣አዳፋ የለበሰ የሰውን
ልጅ ልብስ የምታጥብ እናት፣ጥቂት ጉርሻ ለልጇ ፍለጋ
የጠቆሩ የሰው ገፅ ያጠቆራት እናት፣ ልጇን እንዳዘለች
ውሃ ልትቀዳ፣ በምትቀዳውም ውሃ የድህነት እድፏን
ልታጥበው ወንዝ ወረደች።የብዙ ሰዎችን ቤት እድፍ
ከዚህ በቀዳችው ውሃ አጥባለች።ጥቂት ሸኸሬታ ብዙ ዳቦ እንዲገዛላት ብርታት የሆናት ይህ ውሃ ነበር።ረዳት ባጣችበት ረዳት የሆናት፣ከውሃነት ባሻገር የመኖሯ ቀመር የነበረው ይህ ውሃ ነበር።

ባይራ ዲጂታል መጽሄት 54 ቅጽ ፪ ቁጥር ፱

በአንቀልባ ልጇን ከጀርባዋ እንዳዘለች ከብዙ ወራት በፊት የአንድ ልጇን አባት በሞት መነጠቋን እያውጠነጠነች ውሃ ልትቀዳ ጎንበስ አለች።ፀሐይዋ ስትጠልቅ ምድር በፅልመት ተዋጠች።ጎንበስ ባለችበት ቅፅበት ያ ብዙ መስዋዕትነት ሲያስከፍላት የነበረው አንድ የቀራት፣አንድም ሺህም፣ልጅም ወንድምም የሆናት ልጇ ካዘለችው አንቀልባ ሾልኮ፣ ማንን ልዋጥ እያለ ሲደነፋ ከነበረው ደራሽ ውሃ ውስጥ ጠለመ።ህሊናም አብሮ ከምድር መጥቆር ጋር አብሮ ጠቆረ።

.
.

ጊዜ አሸለበ...

ሾልኮ የገባው ልጇን ከሞት መንጋጋ ፈልቅቃ ልታወጣው ወደሚደነፋው ወንዝ ተወርውራ ገባች።ድንጋጤ ያጠቆረው አዕምሮ መላምት የለውም። ምላሹ ደመነፍሳዊ ነው።በምናልባት ሩጫ መነሁለል።ከብዙ ትግል በኋላ ደራሽ ውሃው እያግበሰበሰ ሲወስድ ዳር ላይ ወርውሮት የሄደ አንድ የግንድ ጉማጅ ይዛ ተረፈች።ያ የሞት ጥላን ያዘለው እርኩሱ ቀን ልጇን በላው።ህይወት ለማትረፍ ህይወት ገበረች።ነገን ለማየት በዛሬ ተረታች።ምኞቷ እልፍ ርቀትን ከልጇ ጋር መጓዝ ነበር።ህልሟን ቀን አበላሸው።ተስፋዋን ወራጅ ውሃ በላው።እቅዷ በልጇ ነበር።እቅዷ ለልጇ ነበር።እቅዷ ስለልጇ ነበር።ነገ በዛሬ ተዋጠ።ጉማጅ ግንዱ ላይ በደረቷ እንደተኛች ልጇ የሄደበትን መንገድ ተከትላ ሀዘን ያፈላ እምባዋን ጊዜ በወሰደ ጉንጯ ላይ እያፈሰሰች በእይታ ብቻ ሸኘችው።አቅም የከዳው በትንታ ይረታል።

ልቧ ሌላ ሰው ለማዳን ነበር...ግን ሌላ ሰው ሞተባት።

ባይራ ዲጂታል መጽሄት 55 ቅጽ ፪ ቁጥር ፱

ፍርድአወቀ ማሞ(ዶ/ር)

ሁለተኛ እትም ለንባብ በቅቷል

ቀይባህር ሲቀላ ቀይባህር ሲቀላ